እንዲህ እያሉ ማስተማር ጀመሩ፣ «የእግዚአብሔር ስጦታ የሆኑትን ልጆች በአግባቡ ባናሳድግ እግዚአብሔር ይጠይቀናል። ስዚህም እንዲረዳን መጥነን መውሰድ አሰብን እንጂ ማንጋጋት የለብንም።» እያሉ ሲያስተምሩ፣ አንድ ያልተዋጠለት ተማሪ ጥያቄ ጠየቀ፣ <በዘፍጥ. 1÷28 ላይ ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉዋት> ይላል፤ የእርስዎ ትምህርት ግን ብዛት ሳይሆን ቅነሳን ነውና የሚያሳየው፣ ከቃሉ ጋራ አይጋጭም ወይ?» ቢላቸው፣ «ታዲያ እግዚአብሔር ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት ቢል፣ እንዳችን 2፣ እንዳችን 3፣ እንዳችን 4፣ እያደረግን በመተባበር እንጂ አንተ ብቻህን ምድርን ልትሞላ ትፈልጋለህ እንዴ?» ብለው ጥያቄውን በጥያቄ በመመለስ አሳረፉት!

እም ወገኖቼ፣ ዛሬ ጎዳናውን የሞሉትን ልጆች እያሰብንና እያዘንን እንጠንቀቅ፣ ነገ የእኛ ልጆች ተራ እንዳይሆን ማሳደግ የምንችለውን ልጆች ብቻ መጥነን እንውሰድ።

ልጆችን የሚያሳድግ እግዚአብሔር ቢሆንም፣ ኃላፊነቱን ግን ለእኛ ሰጥቷልና፣ ኃላፊነታችንን በአግባቡ እንወጣ። ስለዚህ ጠያቂዋ እኅቴ በግሌ ለእንቺ ያለኝ ምክር፣ ከላይ በተዘረዘረው መሠረት ከጋብቻ በኋላ የእርግዝና መከላከያ መውሰድ ኃጢአት አይደለምና አዕምሮሽ ነፃ ይሁን። ሁለት ዓይነት ክፍል ያላቸው 14 ዓይነት የመከላከያ ዘዴዎች አሉ። ከሕክምና ባለሙያ ጋር በመመካከር ተስማሚውን መጠቀም ተገቢ ነው። ለበለጠ እውቀት ይረዳ ዘንድ አሥራ አራቱን ዓይነት እርግዝና መከላከያ ዘዴዎች እንደሚከተለው አቀርባለሁ። ምክንያቱም የእናትና የልጅ ጤና እንዲጠበቅ ብርቱና ደስተኛ ቤተሰብ ከተፈለገ መፍትሔው አራርቆ መውሰድና የቤተሰብን ቁጥር መመጠን ነው።

ጋብቻ ተመርቀው የማይወጡበት የዕድሜ ልክ ት/ቤት ነው!

የሦስተኛው ዓለም ሕዝቦች አንዱና ዋና ችግር የቤተሰብና የገቢ አለመመጣጠን ነው። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ቤተሰቦች ከእጅ ወደ አፍ ኑሮ ይኖራሉ። በቂ ምግብ፣ ልብስና የጤና እንክብካቤ ማግኘት ስለማይችሉ ለአስከፊ ድህነት፣ ለበሽታና ለድንቁርና የተጋለጡ ናቸው። እነዚህን አስከፊ የሰው ልጅ ዕድገት



እንቅፋቶችን ለመከላከልና ኢኮኖሚውን ለማሻሻል እየተወሰዱ ካሉት እርምጃዎች አንዱ የቤተሰብ ምጣኔ መርሐ ግብርን በሁሉም አገሮች በተቻለ መጠን ተግባራዊ ማድረግ ነው።

በጤናው ዘርፍ አራርቆ ለመውለድ የሚያስችሉ የተለያዩ የመከላከያ ዘዴዎች በየጊዜው በሥራ ላይ እየዋሉ ናቸው። ጊዜያዊና ቋሚዎቹን የመከላከያ ዘዴዎች አሁን እንመልከት።

## ሀ. ጊዜያዊ የመከላከያ ዘዴዎች

1. <u>ፒል</u>፡- ለ28 ቀን የሚያገለግሉ 28 እንክብሎችን የሚይዝና ወሩን በሙሉ በማከታተል የሚወሰድ መድኃኒት ነው። እያንዳንዱ እንክብል ሆርሞን የተባለ ንጥረ ነገር የያዘ ሲሆን፣ ከሴት ማሕጸን እንቁላል እንዳይወጣ የሚከላከል ነው። መድኃኒቱ የሚወሰደው በእያንዳንዱ ቀን በተመሳሳይ ጊዜ ነው። አልፎ አልፎም የጤና መታወክ ሲከሰት ለሐኪሞች በመንገር ሌላ ፒል (መድኃኒት) መለወጥ ይቻላል። ይህ መድኃኒት የሚሰጣቸው ሴቶች በወር አበባቸው ጊዜ የደም ፈሳሽና ሕመም ይቀንሳል።

   -ይህ መድኃኒት ከተወሰደ ከመቶ አንድ እርግዝና ብቻ ሊከሰት ይችላል።

2. <u>የማሕጸን ቆብ</u>፡- ይህ ቆብ መሰል ጎማ ሲሆን፣ የሴት ማሕጸን መከደኛ ነው። አገልግሎቱ የወንዱ ዘር ወደ ሴትዋ ማሕጸን እንዳይገባ መከላከል ነው። ቆቡ የተለያየ መጠን ስላለው ከሴትዋ ማሕጸን ጋር የሚስማማና ሙሉ በሙሉ የሚገጥም መሆን አለበት። ከጸረ ወንዴ ዘር (ስፐርሚሳይድ) ቅባት (ክሬም) ጋር ቢሆን በጣም አስተማማኝ ይሆናል።

   - በዚህ ከሚጠቀሙ ሴቶች መካከል ከመቶ አሥር የሚሆኑ ምንጊዜም ሊያረግዙ ይችላሉ።

3. <u>ኮንዶም</u>፡- ለስ የሆነ በወንዱ ብልት ላይ የሚጠለቅ ከረጢት መሳይ ላስቲክ ነው። አገልግሎቱ በግንኙነት ጊዜ ከወንዱ የሚወጣውን ዘር ወደ ማሕጸን እንዳይገባ መቀበልና በውስጡ ቋጥሮ መያዝ ነው። እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ በሴትዋ

ብልት ውስጥ የሚገባ ኮንዶም ነው።

- በዚህ ዘዴ ከሚጠቀሙት መካከል ከመቶ ሰባት ሴቶች ምንጊዜም ሊጸንሱ ይችላሉ።

4. <u>አረፋ ወይም ፀረ ወንዴ ዘር (ፎም ወይም ስፐርሚሳይድ)</u>፡- ይህ ግንኙነት ከመጀመሩ በፊት በሴት ብልት ውስጥ የሚጨመር መድኃኒት ነው። የዚህ ዘዴ ዋና ተግባር የወንዱ ዘር ወደ ማሕጸን ደርሶ ከእንቁላል ጋር ከመገናኘቱ በፊት እንዲመክን ማድረግ ነው።

- ይህን ዘዴ ከሚጠቀሙት መካከል ከመቶ ሃያ ሴቶች በማንኛውም ጊዜ ሊያረግዙ ይችላሉ።

5. <u>ሚኒ ፒል</u>፡- ሴቶች ጡት በሚያጠቡበት ጊዜ ጽንስን ለመከላከል የሚወስዱት ነው። ይህ ሆርሞን ተሸካሚ መድኃኒት እንቁላል ከእቫሪ እንዳይወጣ የሚከላከልና ድንገት ቢወጣ እንኳ የሴትዋን የማሕፀን አቀማመጥ ለእንቁላል ማረፊያ እንዳይመች የማድረግ ባሕሪ አለው።

- የሚያጠቡና ይህን ዘዴ ከሚጠቀሙት ሴቶች ከመቶ ሁለት ብቻ በማንኛውም ጊዜ መጸነስ ይችላሉ። በደንብ የሚያጠቡ እንዲያውም ለብዙ ጊዜ ጽንስን ላያዩ ይችላሉ።

6. <u>መርፌ</u>፡- ይህ ቀላልና ተወዳጅ መከላከያ ዘዴ ነው። የመከላከያ መርፌ የምትወጋ ሴት ለሦስት ወራት ፈጽሞ ልትጸንስ አትችልም። አንዳንዴ የጤና መታወክና የወር አበባ ጊዜ መዛባት ሊያጋጥማት ይችላል።

ይህን የመከላከያ ዘዴ ከሚጠቀሙት ሴቶች መካከል ከመቶ አንድ የመጸነስ ዕድል ሊያጋጥማቸው ይችላል።

## የተፈጥሮ መከላከያ ዘዴዎች

7. <u>ጡት ማጥባት</u>፡- ልጅን ጡት ማጥባት ለጤና እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ለልጅዋ ሌላ ወተት ወይም ምግብ ሳትሰጥ ጡት ብቻ የምታጠባ ሴት ለስድስት ወርና ከዚያም ለበለጠ ጊዜ



ሳታረግዝ ትችላለች። ሆኖም፣ አንዳንዴ የመጀመሪያው ስድስት ወር ካለቀ በኋላ የወር አበባዋም ባይመጣ ጽንስ ልትይዝ እንደምትችል ማወቅ ይኖርባታል።

ጡት ማጥባት አራርቆ ለመውለድ ከሚረዱት ዘዴዎች አንዱ መሆኑን አውቀው እናቶች ልጆቻቸውን ጡት ማጥባት አለባቸው።

8. <u>ተፈጥሮአዊ የመከላከያ ዘዴ</u>፡- ይህንን ዘዴ ለመጠቀም ባልና ሚስት የወር አበባ የሚመጣበትንና የሚሄድበትን ቀን ጠንቅቀው ማወቅ አለባቸው። ጽንስ የሚያዝበትን ጊዜ ካወቁ በኋላ ተመካክረውና ተስማምተው ለአንድ ወይም ለሁለት ሳምንት ያህል ግንኙነት ማቆም ይኖርባቸዋል። ሴትዋ የመጸነሻዋ ወቅት ከመቼ እስከ መቼ ባለው ጊዜ ውስጥ መሆኑን ካወቀች በኋላ በቀን መቁጠሪያ (ካላንደር) ላይ ምልክት በማድረግ ቀኑን መቆጣጠር ይኖርባታል። የጋራ ችግር ስለሆነ አባወራውም በዚህ ሊተባበር ይችላል። አንዳንዴ የሕመም ስሜት ካለ የወር አበባውን ዙር (ሳይክል) ሊያዛባ እንደሚችል ተረድቶ መታከሙ ለጤንነት እጅግ ይጠቅማል። ይህ ዘዴ ትንሽ ውስብስብ ያለ ስለሆነ ጥንቃቄና በቂ ትምህርት ይጠይቃል።

ሳይወልዱ የሚቆዩ ባለ ትዳሮች ሴትዋ ፍሬያማ የምትሆንበትን ጊዜ (የመጸነሻ ወቅት) በሚገባ ጠብቀው ቢገናኙ ልጅ የመውለድ ዕድል ሊኖር ይችላል።

- ይህን ዘዴ ከሚጠቀሙት ከመቶ ሴቶች መካከል እስከ ሃያ የሚደርሱ ሴቶች ሊጸንሱ ይችላሉ።

9. <u>ተእቅቦ (አብስቲነንስ)</u>፡- በቀላሉ ተእቅቦ ማለት ልጅ ላለመውለድ ለተወሰነ ጊዜ ተለያይቶ መተኛት ማለት ነው። ይህ ዘዴ በጥንቃቄ ካልተያዘ በስተቀር ወንዱን ለሌላ ጋብቻ ወይም ዝሙት ሊጋብዝ እንደሚችል ሴቶች ሊዘነጉት አይገባም። ሴት ክርስቲያንም ለጊዜው ለጸሎት ካልሆነ በስተቀር የባልና የሚስት መለያየትን አታበረታታም።

# ሃያ አንደኛ

## ማሕጸኔ በመገልበጡ ምክንያት ልጅ መውለድ አልችልምና ምን ይሻለኛል?

የዚህ መጽሐፍ ዋና ዓላማ ወጣቶች ከጥያቄዎቻቸው ሁሉ ነፃ ሆነውና ከእጮኛቸው ጋር ስትዳራቸው ከጋብቻ በፊት በግልጽነት ተወያይተው ጋብቻቸውን እንዲፈጽሙ ለመርዳት ነው:: ስለዚህ ከጋብቻ በፊት ይህንን ያንቺን ጥያቄ ለጓደኛሽ ንገሪው:: አንዳንድ ጊዜ ከሰማ ይተወኛል፣ በጣም ስለምወደው እና ላጣውማ ስለማልፈልግ በሚል ከንቱ ምክንያት ወጣቶች አንዳንድ ከጋብቻ በፊት መገለጽ የነበረባቸውን ዋና ጉዳዮች በፍርሃት ይደብቁና በሽፍንፍን ይጋባሉ:: «እሰባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመሰሱ» እንደ ተባለው፣ ችግሩ ከመቃሰል ይልቅ ጭራሽ ጉልበት አግኝቶና የተለየ ትርጉም ይዞ ከፊት ቀድሞ ይጠብቃል:: ሲደረስበትም ትዳርን በግጭት ይሞላል፣ ከባሰም ለፍቺ ያደርሳልና ወደዚህ ጉዳይ እንዳትገቢ ዛሬውኑ ጨርሰሽ ትዳርሽን መሥርቺ::

ትዳር የተመሠረተው በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ እንጂ በልጅ ፍቅር ላይ አይደለም:: ከጥንቱም ቢሆን እግዚአብሔር አምላክም ያለው፣ «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፣ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት» አንጂ፣ ልጅ የምትወልድለት እንፍጠርለት አላለም:: ልጆች ከትዳር በኋላ የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው:: እስኪ ልጠይቅሽ፣ አንቺ የምትናገሪው ስለ ማሕጸንሽ መገልበጥ ነው፤ ለመሆኑ ሳይገለበጥ እንዲሁ ብትጋቡና ልጅ መውለድ የማትችዪ መካን ብትሆኚስ ልጅ ስላልወለዳችሁ ትዳራችሁ ሊፈርስ ነው? አይደለም፣ ልጅ የሚሰጥ እግዚአብሔር ነውና በእግዚአብሔር ላይ ታምናችሁ ትዳራችሁን መሥርቱ:: ምን አልባት ይህ ከላይ የተሰጠው ምክር ለጓደኛሽ የማይዋጥለት ቢሆን የሕክምና ባለሙያ አማክሩ:: ይህ ሁሉ ሆኖ አሁንም ቅሬታ ካለ፣ «ሳል ይዞ ስርቆት፣ ቅሬታ ይዞ መጋባት» ውጤቱ አያምርምና አሁኑኑ ማቆም ይመረጣል::



# የውይይት ጥያቄዎች

1. ማሕጸን ሊገለበጥ የሚችልባቸውን ምክንያቶች ዘርዝር?
2. የአንተ እጮኛ ማሕጸኗ ልጅ መሸከም ባይችል ምን ታደርጋለህ?
3. ዘፍጥ. 2:18ን ከልጆች ጋር አያይዛችሁ ተወያዩበት?
4. ይህቺ ልጅ ካገባች በኋላ ለባሏ ብትነግረው ባለቤቷን ምን ማድረግ አለበት?
5. ይህቺ ልጅ ከቤተሰቧና ከቤተ ክርስቲያኗ ጋር በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ማድረግ ይጠበቅባታል?

# ክፍል ሁለት

## ወንዶች የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች

## ሃያ ሁለተኛ ጥያቄ

### ከጋብቻ በኋላ በወሲብ እንጣጣም ወይም አንጣጣም እንደሁ ለማወቅ ቀድመን ብንሞክር እስከ ተጋባን ድረስ ኃጢአት ይሆንብናል ወይ?

ይህ ጥያቄ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሉ ወጣቶች ሲጠየቅ መስማት እጅግ የሚያስደነግጥና የሚያሳዝን መሆኑ አይቀሬ ነው:: ነገር ግን ከጥያቄው አልፎ በተግባርም ጎልቶ መውጣቱ የማይቀር ነውና ከድንጋጤና ከውግዘት ባለፈ ቤተሰብና ቤተ ክርስቲያን በመተጋገዝ ለልጆቻቸው ትምህርትና ምክር መስጠት ያስፈልጋቸዋል:: ስለሆነም፣ ወጣቶች ከዚህ በታች ያለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርትና ምክር ልብ በማለት ሕይወታቸውን በቅድስና ሊመሩ ያስፈልጋል:: ምክንያቱም ከጋብቻ በፊት የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የኃጢአት ውድቀት ነው እላለሁ:: ኃጢአት ውድቀት ብቻ ሳይሆን፣ ራሳችንንም ባልተዘጋጀንበት ኃላፊነት ውስጥ ይጨምራል:: ሐዋርያው ጳውሎስ ለወጣቱ መጋቢ ለጢሞቴዎስ በ1ኛ ጢሞ. 4÷11-12 ላይ እንዲህ ሲል መክሮታል፣ «... በቃልና በኑሮ፣ በፍቅርም፣ በእምነትም፣ በንጽሕናም ለሚያምኑቱ ምሳሌ ሁን::»

ስለሆነም ወጣቶች በቅድመ-ጋብቻ ኑሮአቸው ንጹሕ እንዲሆኑና ምሳሌነት የሞላበትን ኑሮ እንዲኖሩ መርዳትና ማበረታታት ይገባናል:: በተለይም «በንጽሕና» የሚለው ቃል ጢሞቴዎስ ከወጣቶች ጋር ሊኖረው ስለሚገባ ግንኙነት እና ወጣቶችም እርስ በርሳቸው ሊኖራቸው ስለሚገባ ግንኙነት ያመለክታል::

መጽሐፍ ቅዱስ ወጣቶች በቅድመ-ጋብቻ ሕይወታቸው ንጹሕ፣ ቅዱስና ብርቱ ሆነው እንዲኖሩና እግዚአብሔርንም በመፍራት እንዲመላለሱ ያሳስበናል::



ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን የንጽሕና አሳብ በማጠናከር በ2ኛ ውም መልእክቱ ወጣቱን መጋቢ፣ «ከክፉ የጉልማሳነት ምኞት ግን ሽሽ፣ በንጹሕም ልብ ጌታን ከሚጠሩ ጋር ጽድቅን፣ እምነትን፣ ፍቅርን፣ ሰላምን፣ አጥብቀህ ተከተል» በማለት ያሳስበዋል (2ኛ ጢሞ. 2÷22)::

የቅድመ-ጋብቻ ማዕከላዊ ትምህርት ንጽሕና /ቅድስና/ ነው:: ወጣቶችን ስለ ንጽሕና ለማስተማር ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል ከማስተማር ይልቅ ሌላ ምርጫ የለም::

የእግዚአብሔር ቃል በመዝሙር 119:9 የሚለን እንዲህ ነው:-

«ጎልማሳ መንገዱን በምን ያነጻል?

ቃልህን በመጠበቅ ነው::»

ይህ የዳዊት መዝሙር «ሃሌሉያ» በሚለው ርእስ ሥር ያለና ትርጓሜውም ምስጋናንና ውዳሴን ያዘለ ነው:: ታዲያ ወጣቶች ጌታን በማመስገን እንዲኖሩበት በቅድመ-ጋብቻ ሕይወታቸው በነፃ ጎዳና እንዲጓዙ የጌታን ቃል መማርና መጠበቅ ይኖርባቸዋል::

መኃልየ መኃልይ 4:12፣ «እኅቴ ሙሽራ የተቈለፈ ገነት፣ የተዘጋ ምንጭ፣ የታተመም ፈሳሽ ናት::» ይህ ንጽሕናና ቅድስናን ከጋብቻ በፊት መጠበቅ እንደሚያሻ የተጻፈ ነው::

በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለው ግንኙነት:- ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን የምትጠብቅ ሙሽሪት ስለሆነች ተውባና ተስማምራ መጠበቅ እንደሚገባት ሁሉ፣ ወጣቶችም በቅድመ-ጋብቻ ሕይወት የየራሳቸውን ሙሽራ በንጽሕናና በጌታ ጸጋ ተውበው ሊጠብቁ ይገባቸዋል::

ስመሆኑ ከጋብቻ በፊት የሚደረግ የግብረ - ሥጋ ግንኙነት የሚያመጣው ችግር ምንድን ነው?

ዝሙት ኃጢአት ስለሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ያጣላል (ዘጸአ. 22÷13-29)::

በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ መንፈሳዊ ውድቀት ያመጣል::

የሴቲቱን የመጨረሻ ዕድል ያበላሻል፡፡

ለኤች. አይ. ቪ በሽታና በግብረ ሥጋ ግንኙነት ምክንያት ለሚመጡ የአባላዘር በሽታዎች ያጋልጣል፡፡

በራስና በኅብረተሰቡ ዘንድ የአዕምሮና የማኅበራዊ ውድቀት ያስከትላል፡፡

እርግዝናን ያስከትልና ውርጃ እንዲስፋፋ ይዳርጋል፡፡

ከጋብቻ በኋላ በሚኖረው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ችግር ያመጣል፣ ይኸውም በፊት የነበሩትን ሰዎች ከዛሬው ጋር በአዕምሮ በማወዳደር የዛሬውን የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደጋ ላይ ይጥለዋል፡፡

የሚጣጣሙ ሰዎች እስኪገናኙ ድረስ ሙከራው በመቶ ቤቶችም ቁጥርም ቢሆን መቀጠሉ አስደንጋጭ ነው፡፡

አስነዋሪ ኃጢአት ነው (2ኛ ሳሙ. 13÷12-13)፡፡

እስቲ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ጽሑፍ እንመልከት፡-

በአሜሪካን አገር ስለ ወጣቶች ያጠና አንድ የሥነ ልቦና ባለሙያ ወጣቶች የሚያዘወትሩአቸው የወሲብ አፈጻጸም ዘዴዎች ብልታቸውን በመነካካት ወይም በማሸት ስሜታቸውን ማነሣሣት፣ የወሲብ ስሜታቸውን እስኪያረኩ ድረስ ከተቃራኒ ጾታ ጋር መላፋትና ሌሊት በሕልማቸው ከሚወዱት ሰው ጋር መገናኘት እንደ ሆነ ተናግሯል፡፡ እነዚህ ነገሮች በኅብረተሰቡ ዘንድ የማይወገዙ ዘዴዎች ናቸው ተብለው ይነገራሉ፡፡ በተጠቀሱት ዘዴዎች ውስጥ ወንድና ሴት በአካል ወሲብን አይፈጽሙም፡፡ አሁን ግን እነዚህም ዘዴዎች እንደ ተራ ነገር ተቆጥረው ከጋብቻ በፊት ወጣቶች ወሲብ መፈጸም እንደሚችሉ ይነገራል፡፡

ኅብረተሰቡ የሚያሳስበው ያልታቀደ እርግዝና እንዳይከሰትና በአባላዘር በሽታ በተለይም በኤድስ እንዳይያዙ ብቻ ነው እንጂ፣ ከጋብቻ በፊት ወሲብን መፈጸም መልካም አይደለም በማለት አይደለም፡፡ ስለሆኑ የአምላካችን የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ከጋብቻ በፊት ስለሚደረግ ወሲብ ምን ይላል?



መጽሐፍ ቅዱስ ወሲብ በጋብቻ ውስጥ ብቻ እንዲደረግ ያስተምራል፡፡ እንደ እግዚአብሔር ቃል ከጋብቻ ውጭ የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ወሲብ ኃጢአት ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን አንድ ወንድ ድንግል የሆነችውን የሌላ ሰው እጮኛ አስገድዶ ቢደፍር፣ በድንጋይ ተወግሮ ይገደል ነበር፡፡ እንደዚሁም ከጋብቻ በፊት ከሌላ ወንድ ጋር በፈቃዷ የተኛች ወይም ሌላ ሰው ሲደፍራት ሲይዛት ለማምለጥ ሙከራ ያላደረገች የታጨች ሴት ልጅ በድንጋይ ተወግራ ትገደል ነበር (ዘዳግ. 22÷13-29)፡፡ ነገር ግን ያላገባ ወንድ ድንግል የሆነችን ሴት አስገድዶ ቢደፍራት፣ ሲያገባት እንደሚገባው ተጠቅሷል (ዘዳግ. 22÷28-29)፡፡ እንዲሁም አንድ ወንድ ያልታጨችውን ድንግል ሴት በማታለል አብሯት ቢተኛ፣ እርሷን ማግባት እንዳለበት ተነግሯል፡፡ ምናልባትም ማታለል የሚለው ቃል የሴቷን ፈቃደኝነት መኖሩን ያመለክታል፡፡ በእንዲህ ሁኔታ ወሲብ የፈጸመ ወንድም የሚገባትን ማጫ ለወላጆቿ በመክፈል ማግባት እንዳለበት ተጠቅሷል (ዘጸአ. 22÷16-17)፡፡ ይህ ሁኔታ ከጋብቻ በፊት ወሲብ መፈጸም ትክክል አለመሆኑን ያመለክታል፡፡ በማስገደድም ሆነ በማሳሳት ባልተጋቡ ሁለት ሰዎች መካከል ወሲብ ከተደረገ፣ ቶሎ ጋብቻ መፈጸሙ የወሲብ ትክክለኛው ቦታ በትዳር ውስጥ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በብሉይ ኪዳን ከጋብቻ በፊት ወሲብ ፈጽሞ ዝም ብሎ አብሮ መኖር አይፈቀድም ነበር፡፡

በአዲስ ኪዳን ሐዋርያው ጳውሎስ ያላገቡ ለምችን፣ «ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና ከዝሙት እንድትርቁ፣ እግዚአብሔርን እንደማያውቁ አሕዛብ በፍትወት ምኞት አይደለም እንጂ፣ ከእናንተ እያንዳንዱ የራሱን ዕቃ በቅድስናና በክብር ያገኝ ዘንድ እንዲያውቅ» (1ኛ ተሰ. 4÷3-4) እያለ ይመክራል፡፡ በዚህ ክፍል ዝሙት የተባለው ባላገቡ ሰዎች መካከል በፈቃደኝነት ላይ ተመሥርቶ የሚደረገውን ወሲብ ያመለክታል፡፡ ጳውሎስ ያላገቡ ሰዎች የራሳቸውን ዕቃ በቅድስናና በክብር መጠበቅ እንዳለባቸው ያሳስባል፡፡ አማኞች እንደ ሌሎች ያላመኑ ለዎች ከጋብቻ በፊት ወሲብ መፈጸም እንደማይገባቸው ያስተምራል፡፡ ጌታ

ኢየሱስም፣ «ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሮአል» (ማቴ. 5÷29) ብሎ ሲናገር፣ «ሁሉ» ማለቱ ያላገቡትንና ያገቡትን ሁሉ ያጠቃልላል። በዚህ ቃል መሠረት ከጋብቻ በፊት ሴትን አይቶ መመኘትም እንደ አመንዝራነት ይቆጠራል። ስለዚህ ወሲብ መፈጸም ቀርቶ ተቃራኒ ጾታን በፍትወት ስሜት መመኘትም ትክክል አይደለም።

ይህ ዓይነት ትምህርት በሚሰጣቸው ጊዜ አንዳንድ ወጣቶች፣ «ሌላዋን ሴት መመኘት ወይም ከሌላ ሴት ጋር ወሲብ መፈጸም ኃጢአት ነው፣ ነገር ግን ከእጮኛችን ማለትም ወደፊት ከምናገባት ሴት ጋር ወሲብ ብናደርግ ምን ክፋት አለው? የጊዜ ጉዳይ እንጂ ባልና ሚስት ነን» ብለው ይከራከራሉ። ይህ አሳብ እውነትነት አለው። ሌላዋን ሴት መመኘትና የራስን እጮኛ መመኘት አንድ ላይሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን እጮኛሞች መሆን ለመጋባት ዋስትና አይደለም፣ መለያየት ሲኖር ይችላል። ወጣቶቹ እንደሚሉት ባልና ሚስት መሆናቸው የጊዜ ጉዳይ ነው። ይህ ተጋቢዎቹ ታሳቢ ባልና ሚስት እንጂ፣ ገና ባልና ሚስት አለመሆናቸውን ያሳያል። ቢፈላለጉም ጊዜው ገና አልደረሰም። የቅድመ-ጋብቻ ጉዞአቸው ሂደቱን አልጨረሰም። ስለዚህ እግዚአብሔር በጋብቻ ውስጥ ማለትም ከሠርግ በኋላ እንዲሆን ያቀደውን ወሲብ ከዚያ በፊት መፈጸም ከእርሱ ዕቅድ ውጭ የተደረገ በመሆኑ፣ ብንቀበልም ባንቀበልም ኃጢአት ነው። ከጋብቻ በፊት የሚፈጸምን ወሲብ ለማጽደቅ የሚደረገው ሙከራ ሁሉ ከእግዚአብሔር ቃል አኳያ ሲታይ ከንቱ ነገር በመሆኑ፣ ተቀባይነት የለውም። የዘመኑ የግብረ ገብ አቋም መለወጥ የእግዚአብሔር ቃል ትክክል አይደለም የሚለውን ነገር ትክክል ሲያደርግ አይችልም። ይህን እውነት ለወጣቶች በምንናገርበት ወቅት በፍቅር ማድረግ ይገባናል እንጂ እንደ ፈራጅ ሆነን መቅረብ የለብንም። የፍቅርና ለስላሳ አቀራረብ እውነትን ለድርድር ማቅረብ አለመሆኑ መታወቅ ይኖርበታል።

ወሲብ ከጋብቻ በፊት ሲፈጸም በትዳር ሕይወት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት አለ? ይህን ጉዳይ በሚመለከት በምክር አገልግሎት ወቅት መነጋገር አስፈላጊ ነው። የቅድመ -ጋብቻ ምክር



በትዳር ላይ ችግር ያመጣል ተብሎ በሚታሰብ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ያተኩራል። ወርዝንገተን የተባለ የሥነ ልቦና ምሁር ከጋብቻ በፊት የሚደረገውን ወሲብ በተመለከተ ሲናገር፣ ተጋቢዎች እርስ በርሳቸው ወይም ከሌላ ሰው ጋር ከጋብቻ በፊት ወሲብ ከፈጸሙ፣ በትዳራቸው ውስጥ ለሚከሰቱ ችግሮች አንዱ መሠረታዊ መንሥዔ ነው። ስለዚህ ከጋብቻ በፊት ወሲብን መፈጸም ለጋብቻ ችግር መሠረት መጣል ነው። ዋልተር ትሮቢሽም በተመሳሳይ ሁኔታ ከጋብቻ በፊት ወሲብ የሚለማመዱ ተጋቢዎች በትዳራቸው ውስጥ ሲያገኙ የሚችሉትን ደስታ አደጋ ላይ መጣላቸው እንደ ሆነ በመናገር ይህን እንዳያደርጉ ይመክራል።[15]

## የውይይት ጥያቄዎች

1. በወሲብ መጣጣምን በአንድ ጊዜ ሙከራ ብቻ ለዘለቄታ ማወቅ ይቻላል ወይ?
2. የቅድመ-ጋብቻ ወሲብ የሚያመጣቸው ችግሮች ምን እንደ ሆኑ ዘርዝር።
3. የቅድመ-ጋብቻ ወሲብ (የመጣጣም ሙከራ) የሚያቆመው የት ላይ ነው?
4. ጋብቻ ክቡር መኝታውም ንጹሕ የሚሆነው መቼ ነው?
5. ከጋብቻ በፊት ወጣቶች እንዳይወድቁ ከወደቁስ በኋላ ምን ማድረግ አለባቸው? በዝሙት ኃጢአት ለወድቁ ወጣቶች ቤተ ክርስቲያን ምን ማድረግ አለበት?

# ሃያ ሦስተኛ ጥያቄ

## የወደድኳትን ልጅ ለትዳር የምጠይቀው ምን ብዬ ነው ?

ትልቁ ነገር እጮኛ ለመያዝና ትዳር ለመመሥረት የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ፍቅር በሁለቱ ተቃራኒ ፆታዎች መካከል መኖሩ ነው። ፍቅር ካለ ደግሞ መንገድ አለ። ጥያቄው

[15] ከበደ በከሬ፣ ጋብቻን እንዴት ልጀምር? 1995 ዓ.ም፣ ገጽ 95-96።

«የወደድኳትን ልጅ ለትዳር የምጠይቀው ምን ብዬ ነው?» የሚል ነው። መዋደዱ ካለ የሚባለው ነገር አይጠፋም። እስቲ ላንተም ሆነ ለመሰሎችህ ይረዳ ዘንድ የሚከተለውን ትምህርት በጥሞና ተመልከቱ። የወደዳችኋትን ልጅ እንዴት እንደምትጠይቁና ከጥያቄ በፊት ምን ማድረግ እንዳለባችሁ በግልጽ ያመለክታችኋል።

## የመጀመሪያው መቅጠር ነው

የሕይወታችንን ያህል እንደ የከበረ ዋጋ ቆጥረን የምንጀምረውን ጋብቻ እንደ አንዳንድ ሰዎች አቃልለን በአጋጣሚና በየመንገዱ ዳር እንጀምረው። ጸልየን ለብርቱ ጉዳይ እንደ ፈለግናት ነግረን ጽድቅንና ቅድስናን በማያሳድፍ ቦታ እንቅጠራት። ሆኖም የቦታ፣ የቀንና የሰዓት ምርጫዎችን ለእርሷ እንስጥ።

## ሁለተኛው ሰዓት ማክበር ነው

በቀጠሯችን ጊዜ ጥያቄ እንዳይፈጥርባት ከተለመደው አለባበሳችን ወጣ ባለ ዝነጣ እንገለጥ። ይልቁን ከቀጠሯችን ሰዓት ዘግይተን እርሷ ቀድማን በመድረሷ ሕሊናዋን እንዳንጎዳ በብርቱ እንጠንቀቅላት። ምናልባትም እርሷ ብትዘገይ ችግር ገጥሟት ወይንም የተፈለገችበት ጉዳይ ቀድሞ ገብቷት እንደ መግደርደር እያደረጋት ሊሆን ስለሚችል እንታገሳት። ስትደርስም በማስመሰል ያልሆነ ፍቅር ትክክል ነው እንጂ ለምን ብለን ለመምከርና ለማስተካከል እንሞክር። በቀይ ካርድ ከጫወታው ሜዳ እንዳታስወጣን ከለመረልን እርሱን ወደ ፊት እንደርስበታለን።

## ሦስተኛው መጠየቅ ነው

ስምተን የምናውቀው «ሆይን ፍቅር» ሲባል ሊሆን ይችላል። እኔ ደግሞ የጀሮም ፍቅር መኖሩን አመላከቼህ አጠያየቅህን ወግ ባለው ሥርዓትና በፍቅር ይሆን ዘንድ አንድ ሴት የነገረችኝን ምስክርነት ቀጥለን እናንብብ። ለእካለ መጠን ደርሼ ለትዳር እየጸለይኩ ሳለ የማውቀውና ይህ ጎድሎታል የማይባል ልጅ «እፈልግሻለሁ» አለኝ ። ደስ ብሎኝ ተቀጣጥረን ስንገናኝ፣ «ይቅርታ ለትዳር ስለ ፈለግሁሽ፣ ጸልየሽ ፍቃደኛ ከሆንሽ እናግሪኝ» አለኝ።



መንፈሳዊና የተማረ ስለሆነ መልካም ባል ሊሆነኝ እንደሚችል ባውቅም፣ አጠያየቁና አቀራረቡ ቀፈፈኝ። ከዚያም በኋላ በጉባኤ በልብስ እየተጋኔጠ እንዳይለት ከሚሽቀረቀር በቀር ቀርቦኝ ምንም አላናገረኝም። ከእርሱ በኋላ ደግሞ በእድሜ ብዙ የሚበልጠኝ ግን እንደ ልጅ የሚቀብጥ ዝቅተኛ ኑሮ የሚኖር ልብስ ስፌ፣ ጸባዩ ሆነ መንፈሳዊ ሕይወቱ ችግር ያለበት ሰው፣ «በፍቅርሽ ድፍን ሁለት ዓመታት ተሠቃየሁ። ከዚህ በላይ መታገስ ስላልቻልኩ ላናግርሽ ደፈርኩ» ብሎ ለጋብቻ ጠየቀኝ። የጠየቀኝ ሳይሆን ያገባኝ ያክል ደንግጬ አንተ ወራዳ በሚል ቃል መዓቱን አወረድኩ። ያንን ሁሉ ሰምቶ ምን ዓይነት ሞዛዛ እንደ ሆነ አይገባኝም ከወር በኋላ መጣ። «ውበትሽን ሁሌ ጠዋት ጠዋት የሚነግርሽ የቤትሽ መስታወት ሳለ፣ እንችም ከኩራት እኔም ጤና ከማጣት ላንተርፍ ነው» ሲለኝ፣ ተፍቼበት ስሄድ፣ «አለቅን እኮ በሰባራ ሽጉጥ» ሲል ሰማሁት።

በአሥራ አምስተኛው ቀን፣ «ይህንን ያክል ከጠላሽኝ፣ በቃ ይቅርታ አድርጊልኝ። ጨብጠሽኝ ብቻ ልሂድ» ቢለኝም፣ ያው ቁጣው አልለቀቀኝም ነበር። እርሱ ግን ባገኘኝ ጊዜ ሁሉ፣ «አንቺን የምቀየምበትና የምጠላበት ልብም አንጀትም የለኝም» ሲለኝ፣ ባልወደውም የእምነት ሰው ከሚሆነው ሥርዓት ውጭ በመሆኔ በሕሊናዬ አወቀስ ነበር። ስለዚህ ስለ ዱርዬ ጸባዩ ብሰማም፣ መቼም አላገባው፣ እጄን በመጨበጡ ይበልጥ ወዶኝ የሚቸገረው እራሱ ነው ብዬ መጨበጥ፣ ቆንጆ መሆኔን ባውቅም፣ ከማንም ወንድ ያልሰማሁትን መወደዴን ከእርሱ ስለምሰማ፣ እርሱን ባላፈቅረውም መደነቁን መስማት ደስ ይለኝ ጀመር። እርሱም በየቀኑ እያገኘኝ እንዲህ እንዲህ እያልን ሳለ አንዴ የት እንደ ሄደ ሳላውቅ ጠፋ። እኔም በእኔው ፍቅር ታምሞ ተኝቶ ይሆን፣ በእኔ ትዕቢት ትዕግሥቱ አልቆ በሌላ ሴት ተክሶ ይሆን፣ ምኑ ቅጡ፣ የማላስበው የለም። ሌሊት ሁሉ እንቅልፍ ሳጣ የዚያን ጊዜ ነው ለካ ሳይታወቀኝ የወደድኩት መሆኑ የገባኝ።

«ለትዳር በልቤ የነበረው ያኛው ልጅ ደግሞ ለጠብቀው ቆይቼ ከአምስት ወራት በኋላ አመንገድ አቆመኝ። ከዚያም እንደ በፊቱ በመገማጨጭ፣ «አልፈልግም ማለት እኮ መብትሽ ነው። ምን

አስጨነቀሽ?» አለኝ። እንደሚወደኝ እያወቅሁ እኔም ያንን ያህል ብጠብቀውም የተናገረው አነጋገሩና አቀራረቡ ስለ አስጠላኝ፣ «በቃ አልፈልግም» ስለው፣ ለውም ስለ መጣብን ተለያየን። አቤቴ ገብቼ፣ «ለምን እንዲህ አልኩት?» የሚል ጸጸት ሲይዘኝ፣ መልሼ፣ «እርሱስ ለምን እንዲህ ያለ ያልተመረጠ ቃል ይናገራል፣ ምናለበት የዚያኛውን ጥበብና እንደበት ቢሰጠው በማለት እራሴን አጽናናሁት፣ ከዚያ ወዲያ አልተገናኘንም። ይህኛው የጠፋብኝ ለካ ክፍለ ሃገር ሰው ታሞበት ኖሮ ከሁለት ሳምንት በኋላ ሲመለስ ግንኙነታችን በአዲስ መልክ ቀጠለ።

«አንተ ሰታስተምር፣ ወንዶች ዓይናችሁን ሴቶች ደግሞ ጆሯችሁን ከማይገባ ለው ጠብቁ የምትለው ደርሶብኝ፣ ከዚህኛው ጋር ግንኙነታችን ጠንክሮ እንደማይረባኝ ባውቅም አፈቀርኩትና አገባሁት። እናም ለአንድ ልጁ ብዬ ብታገስም፣ ማንንም ሴት ማጥመድ ችሎታ ካለው ከዚህ ሰው ጋር መቀጠሉ የማይዘለቅ ሆነብኝ። ስለዚህም እንደምታውቀው ከአራት የቁስለት ዓመታት በኋላ ተለያየን። ምን ዋጋ አለው፣ ከሌሎች አልማር ብዬ ሕይወቴን ከፍዬ በመማር አሁን ለሌሎች አስተማሪ ሆንኩ።» ብላ በጸጸት አወጋችኝ። ጥንትም እኮ፣ «አፍ ያለው ያግባሽ፣ ከብት ያለው?» ለሚል ጥያቄ፣ «አፍ ያለው» አለች ይባላል። ከዚህ ተምረን ለሚስትነት ለንጠይቃት ፍቅራችንን ደብቀን እግዚአብሔር ሰላለኝ ነው በማለት በእግዚአብሔር የማሳበብን የብዙዎችን ስሕተት እኛም ሳንደግም እንደምንወዳት በግልጽ እንንገራት።

እንዲህም ስለ ተባለ ታዲያ ልቧን ለማማለል ብለን ያልሆነውን (የባጡን የቆጡን) በመጨማመር አናብዛው። አክብሮትን በተላበሰ አነጋገር ክቡር ለሆነው ትዳር ያለብናት መሆኑን መግለጽ ጥሩ ነው። የምትጠይቀን ጥያቄ ቢኖራት፣ የምንመልስላት መልስ ወይም እኛ መናገር የፈለግነው ቢኖር ውሸት አንቀላቅል። እውነት ቢሆንም እንኳ፣ እሺ እንድትል ብለን ዝም ብለን ከመቀላቀል እንቆጠብ። እሺ ለመባል ብቻ እራስን ሳናዘጋጅ ምላሿ ተቃራኒ ቢሆንም፣ ተስፋ መቁረጥ ሳይታይብን በሰላም እንሸኛት። ለእሺና እምቢ የምታቅማማም ከሆነ፣ ወይንም ለምላሿ ቀን የምትቀጥረን



ከሆነ፣ ዛሬውኑ መልስ ካላገኘን የምንፈነዳ ይመስል ግድ ብለን አንወጥራት። በደስታ እንሰነባበት እንጂ።

## አራተኛው ምላሽ መቀበል ነው።

የጠየቅናት ዕለት ፈርታ፣ ደንግጣ፣ ተግደርድራ፣ ወይንም አልታያት ብሎ አሉታዊ ምላሽ ልትሰጠን አልያም ያለ ምላሽ በእንጥልጥል ልንለያይ እንችላለን። እንዲህ ሲሆን በዚያው ደንብረን አንጥፋ። ከወር በኋላ መለስ ብለን እናነጋግራት። ሌላ ቀጠሮ ከሰጠችንም፣ አይክፋን፣ መግደርደር ይዟት ነውና ለዚህም ፈቅደን እንታገስ። ይህ ሁሉ ሆኖ፣ አይሆንም ብላ ከጸናች፣ ነጋ ጠባ መግቢያ መውጫ በማሳጣት እየተከታተልን መብቷን በመጋፋት አናስጨንቃት። ሚስታችን እርሷ ላትሆን ስለምትችል፣ የእኛ የሆነችውን እግዚአብሔር እንዲያመላክተን በጸሎት መትጋትና እራሳችንን ማዘጋጀት ይሻላል። ምላሿ እሺ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ይመስገን፣ ቀጣይ ሕይወታችንን እንደ እግዚአብሔር ቃል ገርተን ለጋብቻ መብቃት ነው።[16]

ለበሰለ ግንዛቤ ይረዳችሁ ዘንድ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን የእጮኛ አጠያየቅ ዘዴዎች ተከተሉ:-

1. የምትወዷትን ልጅ ከአቅም በላይ ካልሆነ በስተቀር በሦስተኛ ሰው አትጠይቁአት። ይህ ዓይነት አካሄድ ሁለት ችግሮችን ይወልዳል:-

   የላክነው መልእክተኛ /ሦስተኛ ሰው/ ልጅቷን ለራሱ ሲያደርጋት ይችላል፤ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ብዙዎች ተጎድተዋልና።

   ምን አልባት ሴቲቱን ለእኔ ፍጹም ፍቅር የለውም ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርሳት ይችላል።

2. እስከ አሁን የተዋጣለት የእጮኛ አጠያየቅ ዘዴ ይሄ ነው ባይባልም፣ ከላይ እንደ ተባለው በግንባር ሄዶ በተዋቡ የቃላት አቀራረብ መጠየቅ ግን ስኬታማ ተመራጭ አጠያየቅ መሆኑን ማወቅ ይገባናል።

[16] ሐዋርያ ዘላለም አበበ፣ ቅድመ ጋር ብቻ ጋብቻ፣ 1997 ዓ.ም፣ ገጽ 130-134።

3. በግንባር ሄዶ ለመጠየቅ አቅም ካልተገኘ ደግሞ፣ በደብዳቤ ጽፎ ራሱ ከጉዳዩ በእጅ በመስጠት መጠየቅ ተገቢ ነው::

በመጨረሻም፣ ለሁለቱም ጾታ የምመክረው፣ ጀምራችሁ ያልጨረሳችሁት የእጮኝነት ጥያቄ ወይም ምላሽ እንዳይኖር ተጠንቀቁ:: እኅቶች በአራት አምስት ወንድ ከዚያም በላይ ከዚያም በታች ተጠይቀው መልስ ሳይሰጡ ይቆያሉ:: ወንድሞችም እንዲሁ የጠየቋቸውን ምላሽ ሳያገኙ ሌላ ጨምረው ይጠይቃሉ:: ይህ ዓይነት አካሄድ ድንገት የሚፈነዳ ቦንብ እንደ መቅበር ነውና፣ እየጨረሳችሁ መሄዱ መልካም ነው:: በትዳር አጠያየቅ ላይ ፍጹምነት ባይኖርም፣ እየጨረሱ /እያጣሩ/ መሄዱ ግን ጠቃሚ ነው::

## የውይይት ጥያቄዎች

1. የወደዳችኋትን ልጅ ለእጮኝነት ምን ብላችሁ እንደምትጠይቁ እስቲ ተነጋገሩበት::
2. ስንት ዓይነት የእጮኝነት አጠያየቅ መንገዶች አሉ?
3. ለእጮኝነት የጠየቅሃት ልጅ እምቢ ብትል ምን ማድረግ አለብህ?
4. በርከት ያሉ ቁጥር ያላቸውን ሴቶች መጠየቅ፣ እና በርከት ላሉ ወንድሞች የትዳር ጥያቄ ምላሽ ሳይሰጡ መቆየት የሚያመጡት ችግር ምንድን ነው?
5. የወደድኳትን ልጅ በሦስተኛ ሰው ማስጠየቅ ምን ችግር ያመጣል?

# ሃያ አራተኛ ጥያቄ

## እጮኝነት የሚፈርስባቸው ምክንያቶች አሉ ወይ?

እጮኝነት የሚፈርስባቸውን ምክንያቶች ከማየታችን በፊት እጮኝነት/መተጫጨት/ ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስን ዋቢ በማድረግ እስቲ እንመልከት:-

ትጭጭት አንድ ወንድና አንዲት ሴት ለመጋባት የሚፈጽሙት የመጀመሪያ ሥርዓት ነው:: ትጭጭት ለመጋባት ተስፋ



መስጣጣት ነው:: አንዱ በሌላው ላይ ትኩረቱን መጣሉንና ዕድሜ ልክ ከእርሱ ወይም ከእርሷ ጋር ለመኖር የሚያደርጉት የመጀመሪያ ምዕራፍ ነው:: መተጫጨት ከተስፋ መስጣጣትም የበለጠ ራስን መስጠት ያለበት ሂደት ነው:: ከመተጫጨት በኋላ በሁለቱ መካከል ጠንካራ ግንኙነት ይጀመራል:: ሆኖም፣ መተጫጫት ቃል መገባባት እንጂ መጋባታቸውን አያመለክትም::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እጮኛ እንደ «ሚስት» ተጠቅሳለች፤ «ማናቸውም ሰው ድንግልና ያላት ልጃገረድ ቢያጭ፣ ሌላ ሰውም በከተማ ውስጥ አግኝቶ ከእርሷ ጋር ቢተኛ ... ሰውየውም የባልንጀራውን ሚስት አስነውሮአልና...» (ዘዳግ፡ 22:23-24) የሚለው ቃል፣ እጮኛ እንደ ሕጋዊ ሚስት ትቆጠር እንደ ነበር ያመለክታል:: በዚህ ሁኔታ ስንመለከት፣ መተጫጨት ሕጋዊ መልክ ስላለው፣ የእጮኛሞች መለያየት እንደ «ፍቺ» ይቆጠር ነበር:: ለምሳሌ:- ማርያም ኢየሱስን በፀነሰች ጊዜ ዮሴፍ በስውር ሊተዋት ወይም ሊፈታት እንዳሰበ ከማቴ. 1:19 እናነብባለን:: እጮኛ እንደ ሕጋዊ «ሚስት» ትቆጠር እንጂ፣ ከጋብቻ በፊት የወሲብ ግንኙነት መፈጸም ፈጽሞ የተከለከለ ነበር::

ሁለት ተቃራኒ ጾታዎች በሚተጫጩበት ወቅት የሽግግር ጊዜ ውስጥ መግባታቸውን ያመለክታል:: ይህ የትጭጭት ወቅት የሽግግር ጊዜ ነው ሲባል፣ ከላጤነት ኑሮ ወደ ትዳር ሕይወት ለመግባት ሁኔታዎች የሚመቻቹበት ነው ማለት ነው:: በመሆኑም፣ ወደሚቀጥለው ቋሚ ኅብረት መሸጋገር የሚቻለው የሚያስፈልጉ ቅድመ - ሁኔታዎች ከተሟሉ ብቻ ነው:: የትጭጭት ወቅት በይፋ የተጀመረ የሁለት ተቃራኒ ጾታዎች ፕሮጀክት ነው:: ፕሮጀክቱ ተገምግሞ ስኬታማነትን የሚያመለክት ሁኔታ ካለው ይቀጥላል፣ አለበለዚያ ግን ይቋረጣል::

ይህ ፕሮጀክት መቼ ይጀመራል? እንዳንዶች እጮኝነት የሚጀምረው አንድ ወንድና ሴት ለመጋባት ከተስማሙበት ጊዜ አንሥቶ ነው ይላሉ:: በዚህ መሠረት፣ የእጮኝነት ወቅት ሁለቱ ከተፈቃቀዱበት ጊዜ ይጀምርና በሠርግ ያበቃል:: አንድ ሰው ይህን አሳብ በመደገፍ የእጮኝነት ጊዜ ሴቷ ተጠይቃ ለጋብቻ የእሺታ

ምላሽ ከሰጠችበት ወቅት ጀምሮ እስከ ጋብቻ ቀን ድረስ ያለውን ጊዜ እንደሚያጠቃልል ተናግሯል፡፡ የእጮኝነት ጊዜ የሚጀምረው እንጋባለን በሚሉ የሁለት ተቃራኒ ጾታዎች ስምምነት ብቻ አይደለም፡፡ ለመጋባት ቃል መግባባት እጮኝነት መጀመሩን አያመለክትም፡፡ እንጋባለን የተባባሉ ወንዶችና ሴቶች እጮኛሞች ናቸው ብሎ መናገር አይቻልም፡፡ ይህ ካልሆነ እጮኝነት መቼ ይጀምራል? እጮኝነት የሚጀምረው እንጋባለን የሚሉ ሰዎች ስምምነታቸውን ለሦስተኛ አካል በሚያሳውቁበትና እውቅና በሚያገኙበት ጊዜ ነው፡፡ ትጭጭት ምስክሮች በተገኙበት ሁኔታ ተጋቢዎች የሚሰጣጡት ቃል ኪዳን ነው፡፡ መተጫጨት ከወንዱና ከሴቷ ስምምነት አልፎ በሌሎች መታወቅ ያለበት ሥርዓት ነው፡፡ ስለዚህ የእጮኝነት ጊዜ የሚጀምረው ተጋቢዎች ለመጋባት መወሰናቸውን ለወላጆቻቸው ወይም ለቤተ ክርስቲያን አሳውቀው እውቅና ከተሰጣቸው ነው፡፡ ወንዶችና ሴቶች የሚኖራቸው ጓደኝነትና ለመጋባት መፈቃቀዳቸው ያለ ወላጆች ወይም/እና ቤተ ክርስቲያን እውቅና እጮኛሞች አያደርጋቸውም፡፡ ከእጮኛሞቹ በተጨማሪ ወላጆች ወይም/እና ቤተ ክርስቲያን የሁለቱ ለመጋባት መስማማት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን መመስከር ይኖርባቸዋል፡፡ ትዳር ያለ ምስክርነት እንደማይጀመር ሁሉ፣ እጮኝነትም እንደዚሁ ነው፡፡ ትጭጭት ሁለቱም ዕድሜ ልካቸውን አብረው ለመኖር የመጀመሪያውን ቃል ኪዳን የሚገቡበት ጊዜ ስለ ሆነ፣ ያለ ምስክር መደረጉ ትርጉም የለውም፡፡

የትጭጭት ዋና ዓላማ ለጋብቻ የተፈቃቀዱት ሁለቱ ተቃራኒ ጾታዎች በይበልጥ እንዲተዋወቁና እንዲቀራረቡ አብረው የግል ጊዜ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው፡፡ ወንድና ሴት ያለ ምንም የወደፊት አብሮ የመኖር ዕቅድ የግል ጊዜ እንዲኖራቸው ማኅበረሰቡም ሆነ ቤተ ክርስቲያን አይፈቅዱም፡፡ ስለዚህ መተጫጨት ለሁለት ተቃራኒ ጾታዎች አብረው ሆነው ለመተዋወቅና ለመቀራረብ ተቀባይነት ያለው ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል፡፡ ይህን የቅድመ-ጋብቻ ግንኙነት የሚያደርጉት በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ውስጥ በመሆን እንደ ሆነ የታወቀ ነው፡፡ ወደ ተነሣንበት ጥያቄ ተመልሰን እጮኝነት የሚፈለግባቸውን ትክክለኛ የሆኑ <u>ስድስት</u> ምክንያቶችን



ከመመልከታችን በፊት፣ አሁንም ስለ እጮኝነት ያለን ግንዛቤ የሰፋ እንዲሆን ሂደቱን እንመለከታለን፡፡

## የትጭጭት ሂደት

የትጭጭት ሂደት ወላጆች ወይም ተጋቢዎች የትዳር ጓደኛ የሚሆን ሰው ከመረጡ በኋላ የሚቀጥለው እርምጃ መተጫጨት ነው፡፡ የመተጫጨት ይዘት የተለያየ ቢሆንም፣ በባህላዊ አሠራር የሚደረገው ሁሉ ተመሳሳይነት ያለው ይመስላል፡፡ ወንዶች በአካባቢ የታወቁ ወይም የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ወደ ሴቷ ወላጆች ይልካሉ፡፡ ከዚያም በመተጫጨት ቀን ወንዱ ከሽማግሌዎችና ከጓደኞቹ ጋር ወደ ሴቷ ቤተሰቦች ይሄዳል፡፡ የቀለበት ሥርዓት የሚፈጸመው በዚያን ዕለት ይሆናል፡፡

ትጭጭት በሚከናወንበት ዕለት አንዳንድ መሠረታዊ የሆኑ ጥያቄዎች በሴቷ ቤተሰቦች ይጠየቃሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ወንዱ ለልጃቸው ሊያደርግ የሚገባውን ነገሮች፣ እንዲሁም በገጠር አካባቢ የማጫ ጉዳይ ይነሣል፡፡ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ማጫ ማለት ወንዱ ለሴቷ ቤተሰብ የሚከፍለው ገንዘብ ነው፡፡ የማጫ መጠን ከቦታ ቦታ ይለያያል፡፡ በአንዳንድ ቦታዎች የማጫ መጠን በኅብረተሰቡ የተተመነ ስለሆነ፣ ከዚያ መቀነስም መጨመርም አይቻልም ይባላል፡፡ ይህ አሠራር በአንዳንድ ቤተ እምነቶችም ዘንድ ተግባራዊ እየሆነ ይገኛል፡፡ በሌሎች ቦታዎች ደግሞ ሁለቱ ተደራድረው የሴቷን «ዋጋ» ይተምናሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ መጠኑን ባያስ-ቀምጥም፣ ማጫ ይከፈል እንደ ነበር ግን ይናገራል (ዘፍጥ. 34:12፤ ዘጸአ. 22:15-16)፡፡ በብሉይ ኪዳን በእስራኤል ሕዝብ ዘንድ ግን የድንግል ማጫ ስንት መሆን እንዳለበት በዘዳግ. 22:29 ላይ ተጠቅሷል፡፡

ለሴቷ ቤተሰብ የሚሰጠው የማጫ መጠን የወንዱን የኑሮ ደረጃ፣ ለሴቷ ያለውን ፍቅርና የእርሷን «ዋጋ» ይገልጻል ተብሎ ይታመናል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሴቷን «ለመግዛት» የሚሰጥ ገንዘብ እንደ ሆነ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ከዚህም የተነሣ ገንዘብ ለማግኘት ብለው ወላጆች ሴቶችን ያለ ፍላጎታቸው ለሀብታም ሰዎች

ይድራሉ::

የማጫው ነገር ፊር ከያዘ በኋላ ሴቷና ወንዱ እንደ ባልና ሚስት ይፈራረማሉ:: ይህ ማለት ከዚያን ዕለት ጀምሮ ሕጋዊ ባልና ሚስት ሆነዋል ማለት ነው:: አንዳንዶች ስተጫጩ በኋላ እስከ ዓመትም ሳይጋቡ ስለሚቆዩ፣ ምናልባት እንዳቸው የትጭጭቱን ውል ለማፍረስ ቢፈልጉ ሂደቱ ውስብስብ ይሆናል:: ጋብቻው ባይፈጸምም፣ እነዚህ እጮኛሞች ሕጋዊ ባልና ሚስት ናቸው:: የቀራቸው የወሲብ·ግንኙነትና እንድ ቤት ውስጥ መኖር ብቻ ነው:: ስለዚህ ከፍቺ ያላነሰ ሂደት ያስኬዳል:: በቤተ ክርስቲያን ደግሞ ተጋቢዎች መስያየት ከፈለጉ ሠርጋቸው እንደ ነገ ሆኖ ዛሬ መስያየት እንደሚችሉ ይታመናል:: ምክንያቱም ከጋብቻ በፊት እንድ ሥጋ ስላልሆኑ፣ በኋላ በጋብቻቸው ውስጥ ችግር ተፈጥሮ ከሚፋቱ፣ ከጋብቻ በፊት ቢለያዩ ይመረጣል በሚል እሳብ ነው:: ይህን· ሁኔታ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ተጋቢዎች የቀለበት ሥርዓት ማድረግ የሚገባቸው ሠርጋቸው እንድ ሳምንት ወይም ቀናት ሲቀሩት እንዲሆን ቤተ ክርስቲያን ታበረታታለች::

በእንዳንድ ቦታዎች ለትዳር የሚፈላለጉ ጓደኛሞች ሲተጫጩ የሚደረገው ፊርማ ለኅብረተሰቡ ቃል ኪዳን መገባባታቸውን ያሳውቃል:: እንዲት ሴት ለአንድ ወንድ ቃል ኪዳን ገብታ ከፈረመችለት ሌላ ወንድ አይነካትም:: በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነትና ልዩ ስፍራ ይሰጣታል:: በተለይ ጠለፋና አስገድዶ መድፈር ባለበት ቦታ ይህ ፊርማ ለሴቷ ጥበቃ ያደርግላታል:: ሌላ ወንድ በእርሷ ላይ የጠለፋ ወይም የአስገድዶ መድፈር ሙከራ ቢያደርግ፣ የሚያስከትልበት ችግር እስከፊ ይሆናል:: ስለዚህ ሁሉም ሰው የታጨችውን (ለአንድ ወንድ የፈረመችውን) ሴት ያከብራታል:: ሆኖም፣ ይህ በሁሉም ቦታ ላይሠራ ይችላል:: ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በአካባቢዋ ዐውድ መሠረት ተስማሚና የእግዚአብሔርን ቃል በማይቃረን ሁኔታ የመተጫጨትን ሥርዓት መፈጸም ትችላለች::[17]

[17] ከበደ በከሬ፣ ጋብቻን እንዴት ልጀምር፣ 1995 ዓ.ም፣ ገጽ 71-73::



ሰው ትዳር የሚመሠርተው የእግዚአብሔር የእምላኩ መልካምና በጎ ፈቃድ ሲሆን ብቻ ነው:: ይህ ካልሆነ ዕድሜንና ጊዜን ከመጨረስ በቶሎ የማቆም ውሳኔ ላይ ተስማምቶ መድረስ ብልህነት ነው:: ምክንያቱም በይሉኝታ ገብቶ በኋላ ከመፋታት ሳይጋቡ መለያየት ይሻላል::

መተጫጨት እንደ ጋብቻ ሊፈረስ የማይችል አንድነት ስላልሆነ፣ ቃል እለመግባባትና አለመማማል መልካም ነው:: ምን አልባት ኅብረቱ እግዚአብሔር ያልፈቀደው ሆኖ ቢፈርስ፣ በመሐላው ኪዳን መርገም እንዳይከተለን ይበጃል:: ይህም ብቻ አይደለም፣ ከጋብቻ በፊት ቀለበት መተሣሰርን፣ እንደ ቀብድ መያዣ አስበን ከሆነ፣ የወርቅ ቀለበት እንኳን ለእጮኝነት ለትዳር መያዣ መሆን አይችልም::

በርካታ ሰዎች ካልተሳካ የእጮኝነት ሕይወት በኋላ የሚኖሩት ኑሮአቸው እሳዛኝና ምስቅልቅል ያለ ነው:: ምክንያቱም እጮኝነትን ያዩት በእንጋባለን እምነት ብቻ ስለ ነበር፣ ያልጠበቁት መለያየት ሲፈጠር፣ እግዚአብሔር ለሁለቱም ሰዎች እንዳደረገው አይረዱም:: የሚረግጡት ምድር እንኳን ሳትቀር የተጸየፈቻቸው፣ እርጉሞች እንደ ሆኑ እራሳቸውን ይቆጥራሉ:: ከዚህም መጥፎ ስሜት የተነሣ አንዳንዶች «ተጋብተው ተፋቱ» መባሉ ይቀላል ይሉና በሕይወታቸው የማይለቃቸውን የሲኦል ኑሮ ይጀምራሉ:: ወይንም «እሾህን በእሾህ ማውጣት ነው» በሚል ፈሊጥ የቀደመው ሰው ከልብ የሚወጣው አዲስ በሚያዝ ሌላ ሰው ነው ይሉና ያልተገባ የእጮኝነት ኅብረት ፈጥረው በማገገሚያነት ይጀምሩና ይቸገራሉ:: እሊያም በመልካም መኖር ካልተቻለ መልካም መለያየት የሚቻል ሆኖ፣ በበቀልና በጥላቻ ተሞልተው እንዳቸው የሌላቸውን በስም ማጥፋት ይሁን በቻሉት መልክ ሲጎዳዱ ይስተዋላሉና እንምስላቸው::

እጮኝነት ማለት ጋብቻ ባለመሆኑ፣ ከመጣ ለማስተናገድ እንዲቻል ለመለየትም ክፍል አዘጋጅቶ መጠበቅ ጥበብ ነው:: ይህ ማለት ግን በየምክንያቱ መለየትን ግብ አድርጎ መራመድ ማለት አይደለም:: ይህ ሁሉ ተደርጎ መለየት ግድ ከሆነ ግን፣

የግሪክ ፈላስፋ የነበረውን ሶቅራጥስ አንዲት ሴት በገበያ አግኝታው፣ «አስቀያሚ ነህ ሰካ» ብትለው፣ እርሱ መልሶ፣ «በአስቀያሚ ዓይንሽ ዓይተሽኝ ነው» አላት ይባላል:: የትዳር ጓደኛ ምርጫን በሌላ ሰው አሳብና ምክር ተመርቶ መወሰን ቆይቶም ቢሆን ችግር ሲፈጥር ይችላል:: አባቶች ሲተርቱ፣ «ሚስትና ምሰሶን ባለቤቱ ይመርጣል» ይላሉ:: አንዳችሁ አንዳችሁን አውጥታችሁና አውርዳችሁ ባያችሁትና በተረዳችሁት አቅጣጫ የበለጠ ለማወቅና ለመረዳት ሞክሩ:: የዕቅዳችሁን ሚና በሚገባ ለመጫወት ራሳችሁን ከሌላ ጋር በማስተያየት ለማወቅ ተጣጣሩ::

አንድ ጊዜ አንድ ትልቅ መሥሪያ ቤት የሚሠራ የመምሪያ ኃላፊ የነበረ ሰው በሰዎች አመለካከት አስቀያሚ የሆነች ሚስት አግብቶ ነበር:: ይህች ሴት በባሏ ስለምትቀና በመኪና ወደ መሥሪያ ቤት አድርሳ በምሳ ሰዓት ተመልሳ ትወስደው ነበር:: ከሰዓት በኋላም ይህንኑ ታደርግ ነበር:: ይህን ሁኔታ የተመለከቱ የመሥሪያ ቤቱ ሰዎች፣ «ይህችን አስቀያሚ ሴት አግብቶ ለምን መከራውን ያያል?» እያሉ ያሙታል:: ሐሜታው እየሰፋ ሄዶ ወደ መምሪያ ኃላፊው ጆሮ ገባ:: ለዚህ መልስ ሲሰጥ አሰቦ በመሥሪያ ቤቱ በየወሩ በሚታተም ዜና መጽሔት ላይ የሚከተለውን ጻፈ:: «ሁለት ጓደኛሞች አብረው ተምረው 12ኛ ክፍልን ከጨረሱ በኋላ አንደኛው የውጭ ትምህርት ዕድል (ስኮላርሺፕ) አግኝቶ ወደ ውጭ አገር ሄደ፣ ሁለተኛው ግን በአገር ውስጥ ሥራ ያዘና ሚስት አገባ:: ወደ ውጭ አገር የሄደው ከአራት ዓመት በኋላ ትምህርቱን ጨርሶ ሲመለስ፣ ጓደኛው በአይሮፕላን ማረፊያ ተገኝቶ ተቀበለው:: በመኪና ውስጥ ሆነው ወደ ቤት በመሄድ ላይ እያሉ ከውጭ የመጣው ጓደኛው፣ «ለመሆኑ ሚስት አግብተሃል ወይስ እንደ እኔው ወንደላጤ ነህ?» ብሎ ይጠይቀዋል:: ጓደኛውም ተዝናንቶ፣ «እኔስ ባለትዳር ነኝ» ይለዋል:: «ለመሆኑ ያገባሃት ቆንጆ ናት?» ብሎ ይጠይቀዋል:: «አዎን፣ ነች» የሚል ምላሽ ይሰጣል:: «ታዲያ፣ ለምን ይዘሃት አልመጣህም?» ብሎ ሲጠይቀው፣ «ጓደኛዬ ከውጪ አገር ይመጣል ብዬ ስላልኳት ወደ ግሮሰሪ ሄዳለች፣ ብዙም ሳትቆይ ትመለሳለች» አለው:: እንግዳውም፣ «ተው አይሆንም በዚሁ መንገድ እርሷንም ይዘናት ወደ ቤት እንግባ



ይለዋል፣» እንግዳ ተቀባይ ጓደኛ:: «አንተን እረፍት መከልከል ይሆናል እንጂ ይቻላል» ብሎ እንግዳውን እንደ ያዘ ሚስቱ ወደ ሄደችበት ገበያ አዳራሽ አመራ:: ከደረሱም በኋላ መኪናቸውን አቁመው የእንግዳ ተቀባዩን ሚስት መፈለግ ጀመሩ:: እንግዳው ከፊት ለፊት የምትመጣውን ሴት ባየ ቁጥር፣ «ሚስትህ ያቺ ናት?» እያለ ሲያስቸግረው፣ «ስደርስ አሳይሃለሁ፣ አትቸኩል» እያለው ሚስቱ ወዳለችበት ስፍራ ደረሱና፤ «በል ከባለቤቴ ጋር ተዋወቁ» ብሎ ሚስቱን አሳየው:: እንግዳው ድንግጥ ብሎ ጓደኛውን በጆሮው፣ «ይህችን አስቀያሚ ነው ያገባሃት?» አለው:: እንግዳ ተቀባዩም መለስ አድርጎ፣ «እርሷስ በጣም ቆንጆ ናት፣ አንተ እኔ ባየሁበት ዓይን ስለአላየሃት ብቻ ነው» አለው:: የመ/ቤቱን ወርሐዊ ጋዜጣ ያነበበ ሁሉ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የመምሪያ ኃላፊውን ማማት አቆመ::[19]

ስለዚህ ወጣቶች የጋብቻ መስፈርታችሁን ሐብት ላይ ወይም ውበት ላይ ብቻ መመሥረት የለባችሁም፣ ምክንያቱም የትዳር መሠረቱ ሐብትም፣ ውበትም አይደለምና:: እስቲ ልጠይቃችሁ ሐብትም፣ ውበትም ኖረው እግዚአብሔርን የምትፈራ /የሚፈራ/ ካልሆነ ጥቅሙ ምኑ ላይ ነው? እንዲያውም ከንቱ ሩጫ ነው:: በምርጫችን ውስጥ እግዚአብሔር ካለበት ግን፣ ውበትንም ሐብትንም እርሱ ይሰጣል::

«ውበት ሐሰት ነው፣ ደም ግባትም ከንቱ ነው፤ እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን እርስዋ ትመሰገናለች» (ምሳሌ 31:30)::

ስለዚህ፣ ወንድሜ ሆይ፣ ልጅቷን በአንተ በራስህ ዓይን አይተህ ወድደሃት ልታገባት ይገባል እንጂ፣ በሐብቷ ብቻ ተስበህ ልታገባት አይገባም:: ምክንያቱም ነገ ሀብቷ ሲያልቅ ፍቅርህም አብሮ ያልቃልና:: ትዳር ደግሞ የዘለቄታ ኅብረት እና አብሮነት እንጂ ለጊዜው እፍ እፍ ብለን የምናናፍሰውና የምናጠፋው አይደለምና ቆም ብለህ ልታስብበት ይገባል::

## የውይይት ጥያቄዎች

1. ሐብትም ውበትም ያላትን ሴት ለማግኘት ምን ማድረግ አለብኝ?

[19] ዮሐንስ ገርማሞና መጋቢ ዶ/ር የሺጥላ መንግሥቱ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጋብቻ፣ 1996 ዓ.ም፣ ገጽ 28-29::

2. እግዚአብሔር የእኔን የትዳር ምርጫ የሚያከብረው እንዴት ነው?
3. በምሳሌ 30:31 ላይ ስላለችው ሴት ተወያዩ።
4. ውበትና ቁንጅና እንደ ተመልካቹ ነው ማለት ምን ማለት ነው?
5. እግዚአብሔርን መፍራት የሌለበት ውበት መጨረሻው ምን ይሆናል?

# ሃያ ስድስተኛ ጥያቄ

## ለጥሎሽ የሚሆን ገንዘብ የለኝምና ምን ባደርግ ይሻላል?

ለዚህ ጥያቄ ቀጥተኛ የሆነ ምላሽ ከመስጠታችን በፊት፣ እስቲ ከአገር ባህል አንጻር የጥሎሽን በጎ ጎንና ጎጂ ጎኑን እንመልከት።

በአንዳንድ አገራት ባህል ሴት ለወንድ ጥሎሽን ትሰጣለች። በእኛ አገር በአንዳንድ ቦታ ወንድና ሴት ለቀሪው ኑሯቸው የሚያጋጩት ሐብትሽ በሐብቴ የሚባል የጥሎሽ ዓይነት አለ። አሁን እየተመለከትን ያለነውና በስፋት የሚታወቀው ጥሎሽ ጥንት መልካምም ጎጂም ጎን ነበረው። መልካም ጎኑ ያ ትዳር ቢፈርስ የሴት ቤተሰብ ጥሎሹን ለባልየው መመለስ ስለሚኖርባቸው፣ ጣልቃ የሚገቡት ባልና ሚስት ባይስማሙም እንኳ የግድ በአንድነት እንዲኖሩ እንጂ እንዲለያዩ አለመሆኑ ነው። ጎጂ ጎኑ ባል ሚስቱን በገንዘቡ የገዛት አድርጐ ስለሚያያትና፣ እርሷም ጥሎሽ በተባለ ዋጋ የተሸጠችበትን መክፈል ያለባት ባለ ዕዳ፣ በቀብድ የተያዘች ዕቃ አድርጋ እራሷን ትቆጥር ስለ ነበር ነው። ከዚህም የተነሣ በጥሎሽ የገዛት ባል እልደላት ሲል፣ የጓዳ ሥራዋን ስታከናውን፦

«አባቴ በላና ሳያየው ልኩን፣
እከፍላለሁ ልጁ የአጥፍ ድርቡን።»

እያለች ታንጎራጉራለች። የባሏ በደል በዝቶ በጣም ያንገሸገሻት ደግሞ፣ ለጥሎሽ የሸጧትን ወላጆቿን ጥሎሽን በማማረር፦



«አባቴን ነበረ በድግር ማለት፣
እናቴን ነበረ በቅርቃር ማለት፣
ሐብት ንብረቱን ቆጥረው ፈቅደው የሰጡት፣
ምን ያድርግ እርሱማ በገዛኝ ንብረት።»

ትላለች። ጥሎሽ አስቆጥሮም ሆነ ጠልፎ ለማግባት ማጣፊያው ያጠረበት ወንድ ደግሞ፣ አብሮ አደግ ወዳጁን ለሴላ ድረውበት ሲያንጎራጉር እንዲህ ይላል፦

«ያላደርግኂትን የወይራ ዘንጌን፣
የጎነጎንኂትን ያንገት ማተቤን፣
ሸጡብኝ ለሃብታም ወይ ደሃ መሆን።»

የአሁን ጥሎሽ ግን፣ በአብዛኛው ስታይታ፣ ለቪዲዮ ማድመቂያና ለልጆች ማስታወሻ እንጂ ያንን ጉልበትና አቅሙን ያጣ ይመስላል።[20]

እርግጥ ነው፣ አንዳንዶች ድሃ ከመሆናቸው የተነሣ እውነተኛ የሆነውን የልብ ፍቅራቸውን አጥተው ተሰብረዋል። ዛሬ ዛሬ እንደምናየው፣ በባህሉ ጥሎሽ የግድ ካልተሰጠ ቤተሰቦቿ ልጅቷን የማይሰጡ ከሆነ፣ ወንዱ ወደ ሦስት አማራጮች ይገባል።

1. የተጠየቀውን ጥሎሽ መስጠት።
2. ካልቻለ ተበድሮ መስጠት።
3. ሁሉም ካልተሳካ ደግሞ ጠልፎ መውሰድ።

በተለይ በሁለተኛውና በሦስተኛው ተራ ቁጥር ያሉት ፈጽሞ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሌለባቸውና በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ሆነ በአገር ደረጃ መቅረት ያለባቸው ተግባሮች ናቸው። ችግሩን የፈጠረው ታዲያ ጥሎሽ መሆኑን እንርሳ። ሁለቱ ፍቅረኛሞች ከተዋደዱና ባህሉም ጥሎሽን በተመለከተ ብዙ የማይጫን ከሆነ፣ የሚቀርበት መንገድ ቢቀየስስ? በግልጽ ከቤተሰብም ጋር ተወያይቶ ቢቀርና ከጋብቻ በኋላ ስሚሆነው የዘለቄታው ኑሮ ታሳቢ አድርጎ

[20] ሐዋርያ ዘላለም አበበ፣ ትድም ጋር - ብቻ ጋብቻ፣ 1997 ዓ.ም፣ ገጽ 178-179።

የጥሎሹን ወጪ ማዞር ቢቻል ብልህነት ነው። በአካባቢ ሁኔታ ከባህል አንጻር ወደዚህ ድምዳሜ መምጣት ግን አደገኛና ለወንጌልም እንቅፋት ከሆነ፣ አቅምን ባገናዘበ ሁኔታ ማድረጉ ተገቢ ነው። ይሁን እንጂ፣ ተበድሮ በኋላ ወደ ግጭትና ለአእምሮ ወደማይመች ነገር መግባት ግን አደገኛ ከመሆኑም በተጨማሪ፣ ለቀጣዩም ትውልድ መልካም ምሳሌ አይሆንም።

አንድ አባት ከሁለት ልጆቹ ጋር የሠርጉን ቪዲዮ ፊልም ሲመለከት፣ የሠርጉ ዋዜማ የተደረገው የጥሎሽ ሁኔታ ልጆቹን ገርሟቸው እንዲህ ብለው ጠየቁት፡- «አባዬ፣ ይሄ ለእማዬ የሰጠሃትን ጥሎሽ የአንገት ሃብሉን፣ ብራስሌቱን፣ የእጅ አንባሩንና ቀሚሶቹን የት ነበር የገዛሃቸው? በጣም ያምራሉ፣ ቆንጆዎች ናቸው» ሲሉት፣ አባታቸው ለሚስቱ የሰጣት ገዝቶ ሳይሆን ከጓደኞቹ ተበድሮ ነበርና፣ ለልጆቹ የሚመልሰው ምላሽ አሳፍሮት፣ «የት እንደ ገዛሁት እናንተን አያገባችሁም፣ ዝም ብላችሁ ፊልሙን ተመልከቱ፣» ብሎ ለልጆቹም ሆነ ለእርሱ ሕሊና የማይመች ምላሽ ሰጣቸው። ስለዚህ፣ በኋላ የምናፍርበትን ዛሬ እንዳናደርግ በአቅም መኖርን ልናዳብር ያስፈልጋል። ተባረኩ!

## የውይይት ጥያቄዎች

1. ጥሎሽን በተመለከተ የቤተሰብ ድርሻ ምን ሲሆን ይገባል?
2. ጥሎሽ ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ወይ? እንዴት?
3. ተበድሮ ጥሎሽ መስጠት ጉዳቱ ምንድን ነው?
4. ሁለቱ ፍቅረኛሞች ከተስማሙ ጥሎሽ ቢቀርስ?
5. በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው የሚታየው መጥለፍ ነው ወይስ መጠላለፍ?



# ሃያ ሰባተኛ ጥያቄ

## ማግባት እፈልጋለሁ፣ ግን በአደጋ ምክንያት የወሲብ ብልቴ የለምና ምን ይሻላል?

የእግዚአብሔር አምላካችን ቃል በ1ኛ ቆሮ. 7፥ 3 ላይ እንዲህ ይላል፡- «ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት፣ እንዲሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ።»

እዚህ ላይ አንዱ ትኩረት የምንሰጠው፣ «ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት» የሚለው ነው። የሚገባት ከተባለው አንዱ ደግሞ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ነው። ይህ በማይሟላበት ወይም ፈጽሞ በሌለበት ሁኔታ ከመጀመሪያውም ቢሆን ጋብቻ ተደርጓል ለማለት ያስቸግራል። ምክንያቱም ንጹሕ የሆነውን የጋብቻ መኝታ አላሟላምና። እስቲ እግዚአብሔር አምላክ ከመጀመሪያ ጋብቻን ሲፈቅድ በውስጡ ምን ምንን ማካተት እንዳለበት ያሰበውን እንመልከት ።

ጋብቻ የታቀደው በሰማይ በእግዚአብሔር ነው። ይህ ዕቅድ በምድር ላይ ተግባራዊ እንዲሆን ለሰው ተሰጠ። እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረው፣ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው (ዘፍጥ. 1፥27) እግዚአብሔር ሰውን በጾታ ለይቶ ሲፈጥር፣ ጋብቻን ዋና ዓላማ አድርጎ ነው።

እግዚአብሔር ለሰው ልጅ በጋብቻ ውስጥ ያዘዘው በረከት፡-

1ኛ. ሰው እውነተኛውን ፍቅር እንዲለማመድ (ኤፌ. 5፥28፤ ዘፍጥ. 2፥24-25)።

2ኛ. ዘር መተካት እንዲችል (ዘፍጥ. 1፥ 28)።

3ኛ. የሕይወት ዘመን ጓደኛ እንዲያገኝ (ዘፍጥ. 2፥18፤ ሚል. 2፥ 14) ነው።

እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የተመሠረተ ጋብቻ የጌታ ቃል እንደሚለው አዲስን ሰው ወይም ሕይወትን የሚፈጥር ነው። ይህም ማለት የሁለት ሰዎች በጋብቻ አንድ መሆን ወይም የሰውነት

ክፋይ ወይም አንዱ በሌላው ውስጥ የመገኘት ምሥጢር ነው:: ይህ የሁለት ሰዎች አንድ የመሆን ጉዳይ የሚረጋገጠው፣ «ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፣ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል /ይጣበቃል/» (ዘፍጥ. 2+24፤ ማቴ. 19+5-6፤ ኤፌ. 5+ 3) በሚለው አምላካዊ ቃል መሠረት ነው::

ክርስቲያናዊ ጋብቻ ማለት የአንድ ወንድና የአንዲት ሴት ሥጋዊ ጥምረት ብቻ ሳይሆን፣ የልብና የመንፈስ አንድነት የሚፈጸምበት ምሥጢር ያለው ኅብረት ነው::

ጌታ ኢየሱስ በማቴ. 19+6 ላይ ፈሪሳውያን ፍችን አስመልክተው ያቀረቡለትን ጥያቄ ሲቃወም፣ «ስለዚህ ባልና ሚስት አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም» ብሏል:: ይህም ከጋብቻ በሚገኘው አንድነት በሥጋ፣ በአሳብ/በዓላማና በመንፈስ አንድ የመሆንን ሁኔታ ያመለክታል:: ዋና ዓላማውም ሰው ለምድራዊ ሕይወቱ የሚመቸውን/ የምትመቸውን እውነተኛ ረዳት/ጓደኛ አግኝቶ ዘመኑን በደስታ እንዲፈጽም ነው::

ከዚህ በታች የተጠቀሱት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎች ጋብቻ እውነተኛ በረከትና ደስታ የሚገኝበት እንደ መሆኑ ባል ለሚስት፣ ሚስት ለባል የደስታ ምንጭ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ::

- «እንዲሁም ባሎች ደግሞ እንደ ገዛ ሥጋቸው አድርገው ሚስቶቻቸውን ሊወዱአቸው ይገባል» (ኤፌ. 5+28)::
- «አዲስ ሚስትም ያገባ ሰው ወደ ጦርነት አይሂድ፣. . . አንድ ዓመት በቤቱ በፈቃዱ ይቀመጥ፣ የወሰዳትንም ሚስቱን ደስ ያሰኛት» (ዘዳግ. 24+5)::
- «ከጕብዝናህም ሚስት ጋር ደስ ይበልህ:: እንደ ተወደደች ዋላ እንደ ተዋበች ሚዳቋ፣ ጡትዋ ሁልጊዜ ታርካህ፣ በፍቅርዋም ሁልጊዜ ጥገብ» (ምሳሌ 5+18-19)::[21]

ከላይ እንዳየነው፣ የጌታ ቃል «ከጕብዝናህ ሚስትህ ጋር ደስ

[21] ዳታን ወዳጆ፣ ትዳር ለዘለቄታ፣ ገጽ 4-5::



ይበልህ . . . ጡቷ ሁል ጊዜ ታርካህ በፍቅሯ ሁል ጊዜ ጥገብ» ይላል:: እነዚህ «ደስ ይበልህ»፣ «እርካ»፣ «በፍቅሯ ሁል ጊዜ ጥገብ» የሚሉት ስሜት አነሣሽ ቃሎች በተግባር ላይ ተሟልተው የሚገኙት ባልየውም ሆነ ሚስትየዋ የተሟላ የጾታ አካል ወይም «የወሲብ ብልት» ሲኖራቸው ነው:: ይህ በሌለበት ግን ማስደሰታቸውና ማርካታቸው ቀርቶ በተቃራኒው ማሳዘናቸውና ማበሳጨታቸው አይቀርምና አስቀድመን ልንጠነቀቅበት ይገባል:: በጉዳዩ ላይ ጠያቂው፣ «በአደጋ ምክንያት የወሲብ ብልቴ የለም፣ ግን ማግባት እፈልጋለሁ» ብለሃል:: በእኔ አሳብ ለማግባት የሚያበቃው አንዱና ዋናው መመዘኛ ይኅድልሃልና ከማግባትህ በፊት ቆም ብለህ ልታስብበትና ከእጮኛህ ጋር በግልጽ ስለ ችግሩ ልትመክርበት ያስፈልጋል:: በተጨማሪም፣ የሕክምና ባለሙያ ልታማክር ያስፈልግሃል:: ይህ ሁሉ ሆኖ፣ ችግሩ ሳይቃለል ቀርቶ ብታገባ ግን የትዳርህ እድሜ አጭር እንደሚሆን ከወዲሁ ልነግርህ እፈልጋለሁ:: ሌላው ይህ የወሲብ ብልት አለመኖር ችግር በወንዱ ብቻ ሳይሆን በሴቶችም ላይ ስለሚታይ፣ ለሴቶችም ያለኝ ምክር ለወንዱ እንደ ሰጠሁት ተመሳሳይ ነውና እናንተም ችግሩን ለምታገቡት ሰው ቀድማችሁ ንገሩ፣ በጋራም ሆናችሁ በሕክምና ባለሙያ በኩል መፍትሔ ፈልጉ::

## የውይይት ጥያቄዎች

1. የወሲብ ብልት የሌለው ሰው ትዳር ቢመሠርት ችግሮቹ ምን ሊሆኑ ይችላሉ?
2. ባል ለሚስቱ ሚስት ለባሏ የሚገባውን ያድርጉ ማለት ምን ማለት ነው?
3. እግዚአብሔር ጋብቻን ካቀደበት ዓላማዎች ሦስቱን ጥቀስ?
4. የወሲብ ብልት /የጾታ አካል/ የሌለው ሰው በሕክምና ሊረዳ አይችልም ወይ?
5. የወሲብ ብልት የሌለው ሰው የወሲብ ስሜት አለው ወይ? ካለውስ ምን ያድርግ?

# ሃያ ስምንተኛ ጥያቄ

## ማግባት ብፈልግም፣ የትዳር መምረጫ መስፈርቴን የምታሟላ ወጣት አጥቻለሁና ምን ባደርግ ይሻለኛል?

ይህንን ጥያቄ አብዛኞች ወጣቶች ይጋሩታል። አንዳንድ ጊዜ የትዳር ጓደኛ ከማይገኝባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተጠቃሽ ሆኖ የሚቀርበው የቲዳር ጓደኛ መምረጫ መስፈርት መኖር ነው። ሆኖም፣ መስፈርቱ ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን ይገባል። አንዳንድ ጊዜ መስፈርቶቻችን እኛ መስፈርት አውጪዎቹ እንኳን ልንደርስባቸው የማንችል ይሆናሉ። «ምላጭ እበጠ፣ በምን ይበጣ » እንደሚለው ብሂል፣ በመስፈርቶቻችን እራሳችን በራሳችን እንቸገራለን።

ሰባኪው ትዳር ያልመሠረቱ ወጣቶችን ሰብስበው እጮኛ እንዴት መያዝ እንዳለባቸው ሲያስተምሩ፣ «ወጣቶች፣ እጮኛ ስትመርጡ መመዘኛ /ክራይቴሪያ/ አታብዙ፣ እግዚአብሔር የሚያስቀምጠው የመጀመሪያ መመዘኛው ክርስቲያን ከክርስቲያን ጋር መጋባት አለበት የሚል ነው። ደግሞ ልብ በሉ፣ ፍጹም የሆነች ሚስት /ባል/ እናገኝም ፣ የምናገኘው አንዱ የአንዱን ጉድለት ለመሙላት ነውና ይህንንም አስቡበት፣ አለበለዚያ ፍጹም የሆነ እንከን የሌለው ጓደኛ እየፈለጋችሁ ብትኖሩ አታገኙም፣ እድሜያችሁ አልቆ ሳታገቡ ቆማችሁ ትቀራላችሁ እንጂ።» የሚለውን ትምህርታቸውን ለማስጨበጥ የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

አንድ ወጣት ሳያገባ እድሜው ከወጣትነት ወደ ጎልማሳነት ገፋ። የቤተ ክርስቲያኑ መጋቢ ጠሩትና፣ «ለምንድን ነው የማታገባው? ሥራ አለህ፣ ቤትም አለህ፣ ሁሉ ተሟልቷል፣ ምንድን ነው ችግርህ?» ብለው ቢጠይቁት፣ እንዲህ ብሎ መለሰላቸው። «ከA-Z ያለውን መመዘኛዬን (ክራይቴሪያ) የምታሟላ ሚስት እጣሁ አላቸው።» እርሳቸውም፣ «እስቲ ለመሆኑ ምንድን ነው? ይሄን ከA-Z ያለውን መመዘኛህን ንገረኝ ልረዳው አሉት።» እርሱም «A አክቲቭ፣ B ቢዩቲፉል፣ C ክሪኤቲቭ፣ D ዲለንት፣ E ኢክስለንት፣ F ፋንታስቲክ፣ G ጀንትል፣ H ሃምብል፣ I ኢኖለንት፣ J ጻይንት፣ K ካይንድ. . .» እያለ ሲቀጥል፣ መጋቢው አቋረጡትና፣ «የእኔ ወንድም ይሄን ሁሉ የምታሟላ ሚስት አታገኝም፣ ነገር ግን ጉድለትና እንከን የሌለበትን ክርስቶስን የምታመልክ ሴት እንድታገባ እመክርሃለሁ» አሉት።

አዎ፣ ወገኖቼ ሆይ፣ ባልና ሚስት የሚጋቡት ለመረዳዳት ነው፣ የሚረዳ ነገር የሌላቸው ምንም የማያስፈልጋቸው ከሆኑ መጋባትም አያስፈልጋቸውምና ከእውነቱ እንዳንርቅ።

በመጨረሻም፣ ሚስትን የሚሰጥ እግዚአብሔር ነውና (ዘፍጥ. 2፥ 22) ወደ እግዚአብሔር እንጸልይ። መጸለይም ብቻ ሳይሆን ጸሎትን በተግባር ለማዋል ከጸሎት በኋላ መፈለጋችንንም እናቁም፣ ወይም ዓይናችንን እንክፈት። እግዚአብሔር ሔዋንን ወደ አዳም ሲያመጣት በንቃት ተመልክቶና እግዚአብሔር በሰጠው እእምሮ ተጠቅሞ ስም ያወጣላት አዳም ነውና፣ ወደ ላይ ቀና ብለን ከጸለይን በኋላ ወደ ጎን ዘወር ዘወር ብለን መቃኘትን እንዘንጋ። በዚህም ድርሻችንን እንወጣ።

ሰባኪው፣ «በዚህ ምድር ላይ ስንኖር ሕይወታችንን የሚመራው ብቸኛና እውነተኛ መሪ እግዚአብሔር ብቻ ነው። በእርሱ ፊት በጸሎት ስንቀርብ እርሱ ፈቃዱን ያስታውቀናል፣ ይኸውም የትኛ ውን ሥራ መሥራት እንዳለብን፣ የት አገር መኖር እንዳለብን፣ በየትኛው መንገድ መሄድ እንዳለብንና ማንን ማግባት እንዳለብን። ይህ ምሪት የሚሆነው ግን የእኛንም ድርሻ ስንወጣ ነው። ዳዊት ለጦርነት ሲወጣ፣ ልውጣ ወይ ብሎ ይጸልያል፣ ውጣ ሲለው ይወጣል፣ አትውጣ ሲለው አይወጣም። አንድ ጊዜ «የኮሽታ ድምጽ ስትሰማ ውጣ፣ እኔ ከአንተ ጋር ነኝ» አለው። መስማት የዳዊት ድርሻ ነበር። ሥራ የሌለው ሰው ወደ እግዚአብሔር ቢጸልይ፣ ሥራ መስጠት የእግዚአብሔር ድርሻ ነው። ወጣ እያሉ የሥራ ማስታወቂያዎችን ማንበብና ማጠያየቅ ደግሞ የግለሰቡ ድርሻ ነው። ልክ እንደዚሁ፣ እጮኛ ለሌለው እጮኛ (ሚስት) መስጠት የእግዚአብሔር ድርሻ ነው፣ በፍቅር መጠየቅ ደግሞ የሰው ድርሻ ነው።» የሚለውን ትምህርታቸውን ለማስጨበጥ የሚከተለውን

ምሳሌ ተናገሩ::

አንድ ወጣት ሳያገባ ብዙ ጊዜ ቆየና ወንጌላዊው፣ «ሚስት ለምን አታገባም?» ብሎ ጠየቀው:: እርሱም «እየጸለይኩ ነው» አለው:: ከዓመት በኋላም አሁንም ጠየቀው፣ አሁንም «እየጸለይኩ ነው» አለው:: አሁንም ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ፣ «አሁንም እየጸለይክ ነው?» ብሎ ጠየቀው:: «አዎ፣ እየጸለይኩ ነው» አለው:: «መቼ መቼ ነው የምትጸልየው እስቲ ንገረኝ» አለው:: «ከሰኞ እስከ ሰኞ ወይም ከእሑድ እስከ እሑድ ነው» አለው:: በዚህን ጊዜ ወንጌላዊው፣ «ይሄማ ልጅቷን የምትጠይቅበት ጊዜም የለህም ማለት ነው:: እባክህ፣ ከዚህ በኋላ ከሰኞ እስከ አርብ ጸልይና ቅዳሜና እሑድ ግን ወደ ጎን ዘወር ዘወር ብለህ ተመልከት::» አለው ይባላል::

## የውይይት ጥያቄዎች

1. ሰዎች ሳያገቡ እድሜያቸው የሚያልፈው ለምንድን ነው?
2. የትዳር ጓደኛ መምረጫ መስፈርታችን ምንን ያገናዘበ ሊሆን ይገባዋል?
3. እንከን የሌለው የትዳር ጓደኛ ማግኘት የሚቻለው እንዴት ነው?
4. የትዳር ጓደኛን ለመምረጥ ከጸሎት በኋላ እእምሮን የምንጠቀመው እንዴት ነው?
5. እግዚአብሔር ሔዋንን ወደ አዳም ሲያመጣት የአዳም ምላሽ ምን ነበር? ከዚህ ዛሬ እኛ ምን እንማራለን?

# ሃያ ዘጠነኛ ጥያቄ

## ለትዳር የጠየቅኳት ልጅ ዘመድ ነንና አይሆንም አለችኝ:: ለመሆኑ መጋባት የማይቻልበት ዝምድና እስከ ምን ድረስ ነው? «እስከ እንጅላት»

ጋብቻ የተለያዩ ጾታ ያላቸውና የደም ዝምድና የሌላቸው ሰዎች የሚመሠርቱት የተቀደሰና የተከበረ ዘለቄታ ያለው የሕይወት ጉዞ



ነው:: ታዲያ ይህንን የእድሜ ልክ ጉዞ ለመጀመር ገና ከመነሻው አጣርቶና ተጣርቶ መጀመር የዘላቂነቱን እድሜ ያጠናክረዋልና ሃያ ዘጠነኛው ጥያቄ ተገቢና ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ጥያቄ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ዘመድን ስለ አለማግባት ምን ይላል? በአጭር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ዘመድን ማግባት ዝሙት ነው ወይም ኃጢአት ነው ይላል:: ኦሪት ዘሌዋውያን 18:6-18 ባለው ክፍል ላይ ልናነብ እንችላለን::

በአዲስ ኪዳንም መጥምቁ ዮሐንስን አንገቱን ሊያስይፈው ከቻለው ነጥብ አንዱ ምክንያት፣ «የወንድምህ ሚስት ለአንተ ልትሆን አይገባም» በማለት የዝምድናን ጋብቻ በመቃወሙ ነው::

አንድ ቦታ ለወጣቶች ይህን «ቅድመ -ጋብቻ» የሚለውን ትምህርት ሳስተምር፣ ሃያ ዘጠነኛውን ጥያቄ አንድ ወጣት ጠየቀኝ:: «ዘመድን ማግባት እንደሌለብን አውቃለሁ:: ግን መጋባት የማይቻልበት ዝምድና እስከ ምን ድረስ ነው?» ለዚህ ጥያቄ ከመጽሐፍ ቅዱስ አብራርቼ ካስተማርኩ በኋላ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥቻለሁ:: «ማግባት የማይቻልበት ዝምድና እስከ እንጅላት ድረስ ነው» ብዬ መለስኩኝ:: አባት - እያት - ቅድመ አያት (2ኛው አያት) - ቅማያት (3ኛው አያት)፣ ሽማት (ሽማያት አራተኛው አያት) - ምንጅላት (ምዝላያት) ወይም 5ኛው አያት - እንጅላት (6ኛው አያት) የመጨረሻው ደረጃ ነው:: «እንጅላት» ማለት «ዘሯን አላውቅም፣ ወድጃታለሁና ላገባት ነው» ማለት ነው:: ስለዚህ፣ ወንድሜ ሆይ፣ ከላይ የእግዚአብሔር ቃል ከሚለው በተጨማሪ እስከ እንጅላት ሳትቆጥር ጋብቻ አትመሥርት:: በተጨማሪም፣ ሰው ዘመዱን ቢያገባ ሌላው በሳይንስ የሚያጋጥመው ችግር የጄኔቲክ አለመጣጣም /Genetic Incompatibility / ስለሚኖር በጽንሱ ላይ ችግር ይፈጠራል፣ ከተወለደም ለየት ያለ ነገር ያለው / Abnormal /ይሆናል፣ እስከ ሞትም ያደርሳል::

## የውይይት ጥያቄዎች

1. መጋባት የማይቻልበት ዝምድና እስከ ምን ድረስ ነው?

2. ዘመዳሞች ቢጋቡ ምን ችግር ይፈጠራል?

3. ከዘሌዋውያን 6:6-18 የተማርከውን ተናገር?

4. ዘመዳሞች እንዳይጋቡ ቤተሰብ ምን ማድረግ አለበት?

5. የደም ዝምድና ያላቸው እንዳይጋቡ ከቤተ ክርስቲያን ምን ይጠበቃል?

# ክፍል ሦስት

## ወንዶችም ሴቶችም በጋራ የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች

## ሠላሳኛ ጥያቄ

### ስለ ጋብቻ ማሰብ ያለብኝ መቼ ነው?

ስለ ጋብቻ ማሰብ ያለብኝ መቼ ነው? የሚል እሳብ ወደ አእምሮው የመጣ ሰው አሁን ስለ ጋብቻ ማሰብ እንደ ጀመረ ያመለክታል። ሆኖም፣ የበለጠ ግልጽ ለመሆን በአብዛኛው ወጣቶች ከ18-25 ዓመት ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ ለጋብቻ ሲመራረጡ ይታያሉ። ሆኖም፣ ከ18 ዓመት በታች ስለ ትዳር ማሰብና/ወይም ማግባት አደገኛነቱ ያመዝናልና ባይሆን ይመከራል። ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ቢጋቡ ቤቱ የልጆች ቤት ይሆናል። በልጆች ቤት ውስጥ ደግሞ ግጭት ቢነሣ ጋዝ ጨምሮ ማባባስ እንጂ ውኃ ጨምሮ ለማቀዝቀዝ የሚሞክር ምናልባት ሊገኝ አይችልም። አንተ ትብስ፣ አንቺ ትብሽ መባባሉና መቀባበሉ፣ መከባበሩና ብስለቱ የሚመጣው በእድሜ ከፍ ከማለትም አንጻር ነውና፣ ቸኩላችሁ ወደ ትዳር ለመግባት ባትጣደፉ መልካም ነው። እንዲያውም፣ ከማግባታችሁ በፊት መንፈሳዊ ብስለታችሁ ማደጉ፣ ተማሪዎች ከሆናችሁ ሁለታችሁንም የሚያኖር የገቢ ምንጭ መኖሩን፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታችሁን ከተቻለም ኮሌጅን መጨረሳችሁን እና በማኅበራዊ ኑሮ ኃላፊነት ለመውሰድ መብቃታችሁንና በአካል መጎልበታችሁን ማረጋገጥ ይገባችኋል።

«ዳሩ ግን ማግባት ወደሚገባ እድሜ በደረሱ ጊዜ . . . ይጋቡ»



(1ኛ ቆሮ. 7:36)። በልጅነት እድሜያችን ስለ ጋብቻ በማሰብ የምናጠፋው ጊዜ አልነበረም። እንዲያውም አንዳንዶቻችን ጋብቻን በተመለከተ የሚደረጉትን ንግግሮች እንሸሽ ነበር። የልጅነት ባሕርያቸው አልለቅ ብሏቸው፣ በአካልና በአእምሮ ካደጉ በኋላ፣ ውስጣቸው በዚህ አቅጣጫ «የረዳት ያለ» ብሎ ሲጮህ፣ በአንደበታቸው ግን ስለዚህ ነገር ማንሣትና ማውራት ኃጢአት የሚመስላቸው ጥቂቶች አይደሉም። ይህ የመንፈሳዊ ሕጻንነት ምልክት ነው።

የትዳር ጓደኛ እስክትመጣ ድረስ ማወቅ ከሚገባን ነገሮች እንዱ መቼ መቀበል ወይም ማግባት እንዳለብን ሲሆን፣ በዚህ ርእስ የሚሰጡ አንዳንድ የጋብቻ ትምህርቶች ግን ሚዛናዊነት ይጎድላቸዋል። አንዳንዱ ቶሎ እንድናገባ ሲገፋፋን፣ ሌላኛው ደግሞ «ትዳር እንዲህ ከሆነማ ይቅርብኝ» የሚያሰኝ ትምህርት ያስተምራል። ስለዚህ የጋብቻ አስተማሪዎች የሆንን የራሳችንን መረዳት ወጣቶች ሙሉ በሙሉ እንዲቀበሉ ከማድረግ ይልቅ በዚህ አቅጣጫ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ እውቀት በመስጠት ወጣቶች ለጋብቻ የሚያደርጉትን ውሳኔ ሁሉ አውቀውት እንዲወስኑ ወደ ትክክለኛ መረዳት ለማምጣት መትጋት አለብን።

ወደ ጋብቻ ዓለም ከመግባታችን በፊት ወጣቶች የእድሜ ብቃት፣ የአካል መጎልበትና የአእምሮ ብስለት ሊኖራቸው ያስፈልጋል። በተለይ ሴቶች እድሜያቸው 18 ሳይሞላ ቢያገቡ በወሊድ ጊዜ ከሚያስከትለው ችግር የተነሣ ማግባት እንደሌለባቸው የጤና ባለሙያዎች ይናገራሉ።

### የትዳር ጓደኛ እስክትመጣ - በጸሎት እየተጉ መጠበቅ

«. . . እለምንሃለሁ፤ መንገዴን. . . በፊቴ አቅናልኝ . . . » (ዘፍጥ. 24:12)፣

አንዳንድ ሰዎች የትዳር ጓደኛቸውን ለማግኘት ለብዙ ዓመታት እንደ ጸለዩ ይመሰክራሉ። ይህ ምስክርነታቸው የማይዋጥላቸው ደግሞ፣ «እንዴ ከጸለይንበት አይበቃምን? ለዓመታት ደጋግሞ መጸለይ ለምን አስፈለገ?» ይላሉ። ከዚህ በመቀጠል የትዳር ጓደኛን

## የውይይት ጥያቄዎች

1. መጽሐፍ ቅዱስ ሰው ስለ ጋብቻ ማሰብ ያለበት ዕድሜ መቼ ነው ብሎ ያስተምራል?
2. ከ18 ዓመት በታች ያሉ ወጣቶች ትዳር ቢመሠርቱ ምን ችግር ይገጥማቸዋል?
3. ወጣቶች ትምህርታቸውን ሳይጨርሱ እጮኛ ቢይዙ ምን ችግር አለው?
4. ወጣቶች ማግባት ወደሚገባቸው እድሜ ሳይደርሱ እንዳያገቡ ከቤተሰቡና ከቤተ ክርስቲያን ምን ይጠበቃል?
5. ወጣቶች ማግባት ወደሚገባቸው እድሜ ሲደርሱ እንዳያገቡ ከቤተሰብና ከቤተ ክርስቲያን ምን ይጠበቃል?

# ሠላሳ አንደኛ ጥያቄ

## አንዳንድ ጊዜ በውስጤ የወሲብ ስሜቶች ይሰሙኛልና ምን ላድርግ?

አንድ ጊዜ አንድ ወጣት እንደዚህ ብሎ የጠየቀኝን አስታውሳለሁ፡- «ቀንም ይሁን ሌሊት አልፎ አልፎ በውስጤ የወሲብ ስሜት ወይም ፍላጎት ይሰማኛል:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ በአእምሮዬ በጣም እጨነቃለሁ፤ ኃጢአት የሠራሁም ያህል ይሰማኛ ል:: ብዙ ጊዜ እንዲህ ዓይነት ስሜት ከእኔ እንዲወገድ ጾምና ጸሎት ሁሉ ወስጄ ለአሥራ አምስት ቀን ያህል ጸልያለሁ፣ ነገር ግን ከእኔ ሊወገድልኝ አልቻለምና በጣም ተጨንቄአለሁ:: እግዚአብሔርንም እየበደልኩ ያለሁ መስሎ እየተሰማኝ ነውና ምን ባደርግ ይሻለኛል?»

ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 13:11 ላይ እንደዚህ ይላል፣ «ልጅ ሳለሁ እንደ ልጅ እናገር ነበር፣ እንደ ልጅም አስብ ነበር፣ እንደ ልጅም እቆጥር ነበር፤ ጎልማሳ ሆኜ ግን የልጅነትን ጠባይ ሽሬአለሁ::» በክርስትና ሕይወታችን የበሰለ እያደግንና በእግዚአብሔር ቃል እውቀት እየበሰልን ስንሄድ፣ እግዚአብሔር



በውስጣችን ያስቀመጣቸውን ፍላጎቶችና እኛ ደግሞ በሥጋችን ተመኝተን ከውጭ የምናስገባቸውን መለየት እንችላለን:: እናም እንደ ልጅ ማሰባችንና እንደ ልጅም ማድረጋችን ይቀራል:: በጌታ ቤት ስንቆይ ማስተካከል ያለብንን ማስተካከል አለብን:: እኔም በመጀመሪያ የክርስትና ሕይወቴ ላይ የተረፈኝን ምግብ ለውሾች አልሰጥም ነበር፣ ምክንያቱም «የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ» የሚለውን ቃል ስላነበብኩ:: ግን በኋላ ልክ አለመሆኔን ላውቅ አረምኩ:: የወሲብ ስሜቶች ሊሰሙን አይደለም ኃጢአት የሚሆነው፣ የተሰማንን ስሜት ለማርካት ያለጊዜው በራሳችን (በሥጋችን) መንገድ ወደ ተግባር ስንሄድ ነው እንጂ:: ስለዚህ የወሲብ ስሜት በውስጣችሁ መኖሩ እግዚአብሔር ጤናማ አድርጎ እንደ ፈጠራችሁ የሚያሳይና እንደ ዳዊት «ግሩምና ድንቅ አድርገህ ፈጥረኸኛልና አቤቱ አመሰግንሃለሁ» (መዝ. 138) የሚያሰኝ ነው:: እግዚአብሔር በውስጣችን ያስቀመጠውን መልካም ስሜት ጾምና ጸሎት ይዘን ከእኛ ላይ እንዲወገድልን የምንለምንበት ምክንያት መኖር አይገባውም::

በመጨረሻ፣ ይህን በውስጣችን የሚሰማንን የወሲብ ፍላጎት ገትተን በምኞት ኃጢአት ሳንወድቅ በቅድስና ቆይተን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በሆነው ጋብቻ እስከምንጣመር ድረስ ከጋብቻ በፊት ምንም ዓይነት ወሲብ እንዳንፈጽም እግዚአብሔር በጸጋው እንዲደግፈን በፊቱ በጸሎት ልንበረታ ይገባል:: በተጨማሪም፣ ወጣቶች ራሳችሁን ዘወትር በሥራ፣ በትምህርት፣ በአገልግሎት፣ መጻሕፍትን በማንበብ ልትጠመዱ ይገባል፣ ምክንያቱም ሥራ የፈታ አዕምሮ የሰይጣን ቢሮ ይሆናልና::

## የውይይት ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር በውስጣችን ያስቀመጣቸውን ስሜቶች ማርካት የምንችለው እንዴት ነው?
2. እግዚአብሔር በውስጣችን ያስቀመጣቸውን ስሜቶች በጾምና ጸሎት ማስወገድ የማይቻለው ስለምንድን ነው?
3. ቤተሰብና ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዙሪያ ምን ማድረግ አለባቸው?

4. ሰው በውስጡ ያለውን የወሲብ ስሜት መቆጣጠር የሚችለው እንዴት ነው?

5. አንድ ሰው የወሲብ ስሜቱን ከጋብቻ ውጪ ለማርካት ቢነሣ የሚከተሉትን ችግሮች ዘርዝር?

## ሠላሳ ሁለተኛ ጥያቄ

## የወላጆቼ ዓይነት ትዳር እንዳይገጥመኝ እፈራለሁና ምን ላድርግ?

ከጥያቄው ድባብ እንደምንረዳው፣ የጠያቂው ቤተሰቦች ትዳር ለልጆቻቸው መልካም ምሳሌ ሲሆን እንዳልቻለ ነው:: ይህ ደግሞ በአብዛኛው ገሃድ የወጣና ሲታረም የሚገባው ችግር ነው:: አንድ ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ልጆች በእረፍት ጊዜያቸው ሲጫወቱ አይቼ ጠጋ ብዬ የሚሉትን ለማሁ:: በቁጥር ስድስት ነበሩ:: የባልና ሚስት ጨዋታ ሲጫወቱ ፈልገው ነገር ግን በመሃከላቸው ያሉት ሁለት ወንዶች፣ «ባል አንሆንም» ብለው ሲከራከሩ ሰማሁ:: ራሴን ጠየቅኩ፣ «ለምንድን ነው ሴቶቹ ባል ሁኑ ብለው ሲጠይቋቸው፣ ወንዶቹ ልጆች ለጨዋታ እንኳን ባል አንሆንም ያሉት? ምን አልባት የእነዚህ ልጆች አባቶች መልካም ምሳሌ የሚሆን ባልነት /አባትነት/ አላሳዩዋቸው ይሆናል» ብዬ አሰብኩ:: ልሳሳት እችላለሁ፤ ጉዳዩ በልጆቹ በኩል በጠቅላላው ሲታይ ግን ትክክል ይመስላል:: ምክንያቱም ልጆች ከቤተሰብ ያዩትን በውጪ ያንጸባርቃሉና::

ስለዚህ ወላጆች እና አገልጋዮች ሁሉ የልጆችን ባሕሪ አውቀን መልካም ምሳሌ በመሆን እንድናሳድጋቸውና እንድንመራቸው የሚከተለውን አራት ዓይነት የዕድሜ ደረጃ ትምህርት በጽሞና ማየት ተገቢ ነው::

ወጣቶች እንደ እድሜ ክልላቸው የተለያየ ማንነት ባሕርይ አላቸው:: ስለሆነም በዚህ አገልግሎት ውስጥ ያለን አገልጋዮች ይህን በጥንቃቄ ልንረዳ ይገባል:: ከዚሁ የሚከተለው የዕድሜ አከፋፈል እንድንረዳቸው ይረዳናል::



### ቅድመ-ጉርምስና (Teenager Period) ከ11-14 ዓመት

. የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ምን እንደ ሆነ ለማወቅ በጣም የሚጓጉበትና እንደውም አንዳንዶች ወይም አብዛኛዎቹ የሚሞክሩበት እድሜ ነው::

. ነጻነት በሁሉ አቅጣጫ የሚሹበት ዕድሜ ነው:: የፈለጉበት ቦታ እንዲወጡና እንዲገቡ፣ ከጓደኛቸው ጋርም እንደ ልባቸው እንዲሆኑ የሚፈልጉበት ጊዜ ነው::

. በእነርሱ ላይ ማንም ባለሥልጣን እንዲሆን አይፈልጉም:: ለዚህም ነው በጎዳና ላይ በዚህ እድሜ ክልል ያሉ በርካታ ወጣቶችን የምናየው::

. ከራሳቸው ቤተሰብ ይልቅ የሚመርጡት የእድሜ እኩዮቻቸውን ነው::

. ታዋቂና ዝነኛ ሰዎችን በመልካምም ይሁን በክፉ መምሰል ይፈልጋሉ:: ለምሳሌ:- ማይከል ጃክሰን ታዋቂ ዘፋኝ፣ ደረጀ ከበደ ታዋቂው ዘማሪ፣ ኃይሌ ገብረሥላሴ ታዋቂ ሯጭ፣ ዶ/ር ቢሊ ግርሃም ታዋቂ ሰባኪ፣ እና ሌሎችንም::

. የእምልኮ ጥማትም በውስጣቸው አለ::

. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙዎች ጌታን የሚያገኙት ከ11-20 ባለው የዕድሜ ክልል ነው::

### ጉርምስና /**Adolescent Period**/ 15-18 ዓመት

- ወንዶች በዚህ ዕድሜ በውስጣቸው ትልቅ ለውጥ ይካሄዳል:: ቴስቴስትሮን የሚባለው ሆርሞን በውስጣቸው በመኖሩና በመጎልበቱ ምክንያት:-
- ጠበኛ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ ድምፃቸው ይጎረንናል::
- ጉልበተኛ እንዲሆኑ ያደርጋል::
- ሴቶችን መውደድ ይጀምራሉ፣ ሴጋ (ማስተርቤሽን) ይጀምራሉ/በገዛ እጃቸው ላይ ላሙናና ምራቅ በመቀባትና

በማሻሸት ዘራቸውን ማፍሰስ::

- ጡንቻቸው ይሰፋል፣ ደረታቸው ይሰፋል፣ በፊታቸው ላይ ጢም፣ በብልታቸው አካባቢም ጸጉር ይወጣል::
- የሚሸነፉ አይመስላቸውም::
- ለጋብቻ የመድረስ ምልክቶች ይታይባቸዋል::
- የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ያደርጋሉ::
- የወንዴ ዘር ማየት ይጀምራሉ:: በዚህ ዕድሜ በተኙበት ስፍራ መኝታቸው ረጥቦ ያገኛሉ:: ይህም የሚሆነው በህልማቸው ከሴቶች ጋር የተገናኙ እየመሰላቸው የወንዴ ዘራቸው ከብልታቸው እንዲሁ እየፈሰሰ መኝታቸውን ስለሚያረጥብ ነው:: ይህ በሕሊናቸው ላይ የኃጢአተኛነትንና የበደለኛነትን ስሜት ይፈጥራል:: በዚህ ወቅት የእኛ እርዳታና ምክር ያሻቸዋል:: እንደ ወጣት ከዚህ ስሜት የተነሣ የሰባት ቀን ጾም ጸሎት አውጃ ነበር:: ዳሩ ግን ችግሩ የተፈታው በዚህ ሳይሆን፣ በምክር አገልግሎት ነው:: ራሳቸውን እንዲቀበሉና ይህ ምልክትም ጤነኛና ተፈጥሮአዊ ምልክት እንደ ሆነ ልንገልጽላቸው ይገባል:: አንዳንድ ልጆች እንዲህ ከምረክስ እራሴን ባጠፋስ በማለት በራሣቸው ላይ አሠቃቂ እርምጃ ሊወስዱ ይችላሉ::
- የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን የሚያጠናቅቁበት ዕድሜ ነው::
- ታዋቂነትና ዝነኝነትን ይፈልጋሉ::
- የአምልኮ ጥማት አላቸው::
- ከልጅነት አስተሳሰብ ወደ ተገቢ ውስብስብና ምክንያታዊ አስተሳሰብ ይሻገራሉ:
- ሴቶች እዚህ ዕድሜ ክልል ሲሆኑ ለውጦች በውስጣቸው ይከናወናል:: በእነርሱ ውስጥ ደግሞ የሚጎለብቱት ሆርሞኖች በሁለት ይከፈላሉ:: አንደኛው ኤስትሮጂን የተሰኘው ሲሆን፣ ከዚህ ሆርሞን የተነሣ:-



- ደስታ ይሰማቻዋል::
- ሽንቃጣ ይሆናሉ::
- በራስ መተማመን ይጀምራሉ::
- ከፍተኛ ፍቅር ይታይባቸዋል::
- ሰዎችን ሰይተው ማየት ይጀምራሉ::
- ወንዶችን መውደድና መቅረብ ይጀምራሉ::
- የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ያደርጋሉ::

ሁለተኛው ሆርሞን ፕሮጀስትሮን ይባላል:: ከዚህ ሆርሞን መጎልበት የተነሣ ደግሞ የሚሆኑት ነገሮች የሚከተሉት ናቸው:-

- የእናትነት ባሕርይ መታየት ይጀምራል::
- የሰውነት ልስላሴን ያመጣል::
- እርጋታን ያመጣል፣ የአእምሮ ብስለትም ያመጣል::
- ስሜታቸውን በቀላሉ የሚነካ ያደርገዋል::
- የወር አበባ ማየት ይጀምራሉ፣ በዚህ ወቅት ነጭናጫ ይሆናሉ::
- የማግባትና ልጅ የመውለድ ተፈጥሮአዊ ምልክቶች ይታያሉ::
- ጡታቸው ያጎጠጉጣል::
- በብልታቸው አካባቢ ጸጉር ያበቅላሉ::
- እነዚህ ሁለት ሆርሞኖች በየ15 ቀኑ ከፍና ዝቅ በማለት ይፈራረቃሉ::
- ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የሚጨርሱበትም ዕድሜ ነው::
- የአምልኮም ጥማት አላቸው::

**ቅድመ -ጉልምስና (Young Adult) 19-25 ዓመት**

- ራሳቸውን ጠንክር ላሉ ኃላፊነቶች የሚያዘጋጁበት ጊዜ ነው::

- ለከፍተኛ ትምህርት የሚዘጋጁበትና የሚጨርሱበትም እድሜ ነው (ዲፕሎማ፣ ዲግሪ የመሳሰሉትን)::
- በሕይወታቸው ቋሚ የሚመስሉ ውሳኔዎችን መወሰን ይጀምራሉ፣ ዳሩ ግን በአብዛኛዎቹ ውሳኔዎቻቸው ሳይዘልቁበት ይቀራሉ፣ ለምሳሌ:-
    - የትምህርትና የሙያ መስክ፣ የሚኖሩበት አገር፣
    - የሚያጩት ወይም የሚያገቡት ሰው::
- የግብረ-ሥጋ ግንኙነትን በድብቅ የሚለማመዱበትም እድሜ ነው::
- ለኬታማነት በየአቅጣጫው ይገጥማቸዋል (ለምሳሌ:- በትምህርት፣ በአገልግሎት፣ መዝሙር፣ ሰብከት፣ ቆንጆና መልከ መልካም ሰው በማጨትና በሌሎች የሕይወት አቅጣጫዎች)::
- የሚያመልኩትን በመረዳት ማምለክ ይፈልጋሉ (ያመልካሉም)::
- የአስተሳሰብ ደረጃቸው ውስብስብና ልበ ሙሉነት /ቆራጥነት/ የተላበሰ ነው::

## መካከለኛ ጉርምስና /Middle Adult/ 26 - 35 ዓመት

- ለቋሚና ዘለቄታነት ላላቸው ውሳኔዎች የሚዘጋጁበት ዕድሜ ነው::
- (ለምሳሌ:- - የትምህርት፣ የሙያ መስክ፣ የትዳር ውሳኔ፣ የሚኖሩበትን አገር የመወሰን ጉዳይ)::
- የውሳኔ መቀያየር ብዙ የማያጠቃቸው ዕድሜ ነው::
- መረጋጋት በሁሉ አቅጣጫ ያሳያሉ::
- በቶሎ ማግባትና ማረፍም ይሻሉ /ይናፍቃሉም/::
- በመረዳት ያመልካሉ::
- የአስተሳሰብ ደረጃቸው አጅግ ውስብስብና አውቀትና



ምክንያታዊነት የሞላበት ነው::
- የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ከጋብቻ በፊት የለመዱ ከሆነ በብርቱ ጥንቃቄና ምሥጢር በሰፋት (በተደጋጋሚ) ይፈጽማ::[23]

ከዚህ በላይ እንደ ተመለከትነው፣ ወጣቶች በአራቱም ዓይነት የእድሜ ክፍፍል የተለያየ ባሕርይና ማንነት ስላላቸው፣ እኛም ይህንኑ ተረድተን ይህንን ማንነት ለእግዚአብሔር ክብር፣ ለእነርሱና ለቤተ ክርስቲያን ጥቅምና በረከት ሊያስገኝ በሚችል መንገድ እንዴት ሊያሳልፉ እንደሚገባ ልንመክራቸው፣ ልንጸልይላቸውና መንገድ ልናሳያቸው ይገባል::

### ወላጆች ይህንን ልብ እንበል?

- ልጅ እየተወቀሰ ካደገ ማውገዝን ይማራል::
- ልጅ በጥላቻ አካባቢ ካደገ መደባደብን ይማራል::
- ልጅ እየተፌዘበት ካደገ ዓይናፋርነትን ይማራል::
- ልጅ በሐፍረት ካደገ ጥፋተኝነትን ይማራል::
- ልጅ በመቻቻል ካደገ ትዕግሥተኛነትን ይማራል::
- ልጅ በመበረታታት ካደገ በራስ መተማመንን ይማራል::
- ልጅ በመሞገስ ካደገ ማድነቅን ይማራል::
- ልጅ በአግባብ ካደገ ፍትሕን ይማራል::
- ልጅ ዋስትና ባሰው ኑሮ ካደገ ለውን ማመንን ይማራል::
- ልጅ በተቀባይነትና በወዳጅነት ካደገ በአጠቃላይ ከዓለም ፍቅርን ይማራል::
- ልጅ መልካም ምሳሌነት ባለው ቤተሰብ ውስጥ ካደገ ከዚያ ፈቀቅ አይልም /ምሳ. 22÷6/::

ልጆችም ሆነ ወላጆች ሊያውቋቸው የሚገቡትን አራቱን

[23] ወርቁ ኃ/ማርያም፣ የትድሙ-ጋብቻ ሥልጠና (ያልታተመ ጽሑፍ) 1997 ዓ.ም፣ ገጽ 7::

ዓይነት የልጆች አስተዳደግ ሥርዓት እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡-

1. ከፍተኛ ቁጥጥር ያለበት /አውቶሪቴሪያን/። ዱሳ ጭምር ያለበት፣ ቆላ. 3፥21ን የሚጥስ- እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን የሚል ጭካኔ የሚንጸባረቅበት። በዚህ ጊዜ ልጆቹ የተነፈጉትን ነጻነት በግድ ለማድረግ ይነሣሉ፣ ዐመፀኛም ይሆናሉ።

2. ዝርክርክና ግዴለሽ /ኔግሌክትፉል/። ለልጆች ትምህርት፣ እድገት፣ ጤንነት፣ ወዘተ. . ደንታ የማይሰጥ /ከልጆቻቸው የራቁ/ (1ኛ ጢሞ. 5፥8)።

- ይህ ዓይነት አስተዳደግ ልጆቹ ሲያድጉ የማይታዘዙ ከመንግሥትና ከሕግ ጋር የሚጋጩ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።

3. ልቅ፣ ከመጠን በላይ የሚፈቅድ /ፐርሚሲቭ/። የሚጠይቁትን ሁሉ በማድረግ የሚያቀማጥሉ፣ በቂ ቁጥጥር የማያደርጉና የማይቀጡ።

4. ዲሞክራሲያዊ ወይም ተሳትፏዊ አያያዝ። መወያየት ያለበት፣ ልጆች እንደ ሁኔታው አሳባቸውን የሚገልጹበት፣ ከፍተኛ ፍቅርና መተሳሰብ ያለበትና ሲያስፈልግ በመጠኑ የሚቀጡበት ነው (ምሳሌ 26፥6፤ 15፥28)። ይሄኛው ዓይነት አስተዳደግ ይመረጣል፡-

በሌላ በኩል ልጆች የራሳቸው ማንነት /ስብዕና (ፐርሰናሊቲ)፣ የራሳቸው ስሜት (ፊሊንግ)፣ እና የራሳቸውን የሆነ እኔነት (አይደንቲቲ) እንዳላቸው ማወቅ ለወላጆች እጅግ ጠቃሚ ነው። ቤተሰብን መምራት ቀላል አይደለም፣ በሌላው ዓለም ቤተሰብ እንዴት መምራት እንደሚቻል ለወላጆች ተከታታይ ትምህርት ይሰጣል። መውሰድ ብቻ አይበቃምና ማላደግም እውቀት ይጠይቃል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ይላል፣ በተለይ በምሳሌ መጽሐፍ ጸሐፊው የልጅን ሁኔታ ጠንቅቆ የተረዳ ይመስላል፡-

- «ተስፋ ገና ሳለች ልጅህን ገሥጽ፣ መሞቱንም አትሻ» (ምሳ. 19፥18)።



- «ሕፃንን ከመቅጣት ቸል አትበል፣ በበትር ብትመታው አይሞትምና። በበትር ትመታዋለህ ነፍሱንም ትታደጋለህ» (ምሳሌ 23፡13፥14)። በትር የሚለውን አዲሱ ትርጉም «አርጩሜ» ይለዋል።
- «ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፣ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም» (ምሳ. 22፥6)።
- «ስንፍና በሕፃን ልብ ታስሮአል፣ የተግሣጽ በትር ግን ከእርሱ ያርቃታል» (ምሳ. 22፥15)።
- «በትርና ተግሣጽ ጥበብን ይሰጣሉ፣ ያልተቀጣ ብላቴና ግን እናቱን ያሳፍራል» (ምሳ. 29፥15)።
- «ልጅህን ቅጣ እረፍትንም ይሰጥሃል፣ ለነፍስህም ተድላን ይሰጣታል» (ምሳ. 29፥17)።
- «በብትር ከመምታት የሚራራ ሰው ልጁን ይጠላል፣ ልጁን የሚወድድ ግን ተግቶ ይገሥጸዋል» (ምሳ. 13፥24)።

መጽሐፍ ቅዱስ ለወላጆች ይህንን ቢናገርም፣ በተናደዱ ቁጥር በትር እያነሡ ልጆችን የቁጣ መወጣጫ ማድረግ በተቃራኒው መንገድ እግዚአብሔርን መበደል ሆኖ ሲቆጠር ይችላል። ጌሪ ስሞሊይ የተባሉ የቤተሰብ ተመራማሪ፣ ለንቀጣ እጃችንን እንዳንጠቀም አጥብቀው ያስተምራሉ። ምክንያቱም ልጆች ወደፊት የእጃችንን ጭካኔ ስለሚያስታውሱ፣ በሌላ መቅጫ (በበትር) መቅጣት ይጠቁማሉ። ለንቀጣም ስሕተታቸውን ማላወቅ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ። ቅጣት በፍቅር መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል ብለዋል። በእርግጥ አትቅጡ ብለው የሚያስተምሩም አሉ። ይህ አመለካከት ደግሞ ትውልድ እንዲበላሽ የሚመኝና የሚያደርግ ነው። ይህ ልቅነት በአገራት ላይ የቴክኖሎጂ ሥልጣኔ ቢያመጣም፣ የኅብረተሰብ መዝቀጥ አድርሷል። ለእርምት፣ ለትምህርትና ለግሣጼ የሆነ ቅጣት በትር ብቻ አይደለም። የተለያየ የቅጣት ዓይነት ሊሆን ይችላል። አንድን ልጅ ለብቻው ወስዶ መገሠጽና መምከር በተደጋጋሚም ማረም ጥቅሙ ከፍተኛ ነው። ሁል ጊዜ በትር ነገርን ይሸፍንና ልጁ ድብቅ ባሕሪን እንዲለማመድ

ያደርጋል። በግልጽ መነጋገር ግን ወዳጅነትን ከመፍጠሩም በላይ፣ ልጅን በወቅቱ ማረም ይቻላል። ተሰፋ ሳለ በወቅቱ ማድረግ፣ ሳይከማችና ሳይጠራቀም ነጥብ በነጥብ ማረም ይጠቅማል። አድጎ የተጣመመ ባሕሪ እንዳይኖረው በወቅቱ ለማቃናት ይቻላል። ቀዳ በእርጥብነቱ ካልተጠቀለለ በኋላ ይገርራልና እሺ አይልም።

ከዚህ በተረፈ፣ ወላጆች አድልዎ የሌለበትና የተስተካከለ አስተዳደር በቤተሰብ መካከል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። «በማድላት በቁራሽ እንጀራ መበደል መልካም አይደለም» (ምሳ. 28፥21)። አንድ ጊዜ ያዕቆብ ያደረገውን (ዘፍጥ. 37፥32) ማስታወስ ይጠቅማል። ወንድሞቹ በዮሴፍ ላይ በማደም ሊገድሉት የሞከሩት፣ በኋላም የሸጡት አባቱ የተለየ ሽሚዝ ያለበሰው እንደ ነበር ሁሉ ሳይረዱ አይቀሩም። ወላጆች እንደዚህ ያለ የማበላለጥ ተግባር በልጆች መካከል ማድረግ ፈጽሞ አይጠበቅባቸውም። በአርግጥ ሰው ደካማ ነውና የዚህ ዓይነት አጋጣሚ እንኳን ቢታይ በቶሎ ማረም ይበጃል።

በቅርብ ቀን የመጀመሪያው ልጄ ከአራት ዓመት በፊት የያዘብኝን የአድልዎ ቂም ሲነግረኝ በእንባ ይቅርታ ጠየቅኩት። ነገሩ ትንሽ ቢሆንም የልጅ ጭንቅላት ሊሸከመው የሚችል ሆኖ አልተገኘም ነበር። ትንሽ እኅቱን ሳያውቅ በድንገት በኳስ ይመታትና ይቅርታ እየጠየቃት ሳለ ሮጣ መጥታ ለእኔ በመናገሯ መትቼው ነበር ለካ። ሰመታው ከግድግዳ ጋር ተጋጭቷል። በዚህ ምክንያት ችግሩን ሳልረዳ በቁጣ በመምታቴ ጎድቼው ነበር። «አብዛኛው ቤተሰብ» ልጁን እንደሚወድ እኔም ልጆቼን የምወድ አባት ነኝ ብዬ እገምታለሁ። ልጄም ይህንን የሚረዳ ይመስለኛል። ዳሩ ግን ስሜቱን ስለ ጎዳሁት ለአራት ዓመታት ያህል ቂም ይዞ አንድ ምሽት የመገላለጽ ምሽት ነበረንና እግዚአብሔር ረድቶት ቅሬታውን አውጥቶ ለመነጋገር ቻልን። በግልጽ ባንነጋገር ኖሮ ምን ያህል እንደሚጎዳው መገመት እያዳግትም ነበር። ወላጆች ልጆች ስሜት እንዳላቸው ልብ በሉ፣ ስለዚህ ተጠንቀቁላቸው። ልጆች በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ የሰው ዘር አካልና ውጤት ናቸው።



ምክር ለወላጆች:-

1. እንደየዕድሜያቸው የጸታ ትምህርት ለማስተማር ከልጆቻችሁ ጋር ጊዜ መውሰዱን ችላ አትበሉ።
2. ለልጆቻችሁ ከልጅነት ጀምሮ ሥራ እንዲለምዱ የሥራ በሮችን ከፈቱ እንጂ ሁሉንም በሠራተኛ ብቻ አታሠሩ (የራሳቸውን ልብስ ይጠቡ፣ አልጋቸውን ያንጥፉ፣ መኝታ ቤታቸውን ያጽዱ)። ልጆቻችንን እግዚአብሔርን መፍራትና በሥራ መትጋትን እናውርሳቸው፣ አብረዋቸው ይኖራሉና። የምናወርሳቸው ሐብት ግን አንድ ቀን ያልቃልና።
3. አሉታዊ ተጽዕኖ ያሏቸውን ብሂሎች አትጠቀሙ። (ለምሳሌ:- ልጅ ይሮጣል እንጂ አባቱን አይቀድምም። ልጅ ያቦካው ለእራት አይበቃም። የልጅ ነገር እንዱ ብስል እንዱ ጥሬ።)

ምክር ለልጆች:-

- እናትና አባታችሁን አክብሩ፣ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነውና (ዘዳግ. 5፥16፤ ኤፌ 6፥2-3)።

«ልጄ ሆይ፣ የአባትህን ትእዛዝ ጠብቅ፣ የእናትህንም ሕግ አትተው» (ምሳ. 6፥20)።

«እናንተ ልጆች የአባትን ተግሣጽ ስሙ፣ ማስተዋልንም ታውቁ ዘንድ አድምጡ» (ምሳ. 10፥1)።

«ጠቢብ ልጅ አባቱን ደስ ያሰኛል፣ ሰነፍ ልጅ ግን ለእናቱ ኀዘን ነው» (ምሳ. 10፥1)።

«ባለ አእምሮ ልጅ የአባቱን ተግሣጽ ይሰማል፣ ፌዘኛ ግን ተግሣጹን አይሰማም» (ምሳ. 17፥6)።

«ሰነፍ ልጅ ለአባቱ ጸጸት ነው፣ ለወለደችውም ምሬት ነው» (ምሳ. 17፥25)።

«ሰነፍ ልጅ ለአባቱ ኀዘን ነው» (ምሳ. 19፥13)።

«አባቱን የሚያስከፋ እናቱንም የሚያሳድድ የሚያሳፍርና ጎሰቋላ

ልጅ ነው» (ምሳ. 19÷26)።

«አባቱን ወይም እናቱን የሚሰድብ በድቅድቅ ጨለማ መብራቱ ይጠፋል» (ምሳ. 20÷20)።

«የወለደህን አባትህን ስማ እናትህም ባረጀች ጊዜ አትናቃት» (ምሳ. 23÷22)።

«ከአባቱና ከእናቱ የሚሰርቅ ኃጢአትንም አልሠራሁም የሚልም የአጥፊ ባልንጀራ ነው» (ምሳ. 28÷24)።

«በአባቷ የምታላግጥ የእናቷንም ትእዛዝ የምትንቅን ዓይን የሸለቆ ቁራዎች ይጎጠጉጧታል፣ አሞራዎችም ይበሉዋታል» (ምሳ. 30÷17)።

ልጆች ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሲኖሩ አንዳንድ ጊዜ ቀንበር ሊከብዳቸው ይችል ይሆናል። ቢሆንም፣ በተለይ ጌታን የሚያውቁ ልጆች በመታገሣቸው የቤተሰባቸውን ሕይወት የሚታደጉበት ወቅት አለ። ወላጆቻቸውን በተለያየ ተግባር ቢረዱ በረከትን ያገኛሉ። ነገር ግን የባህል ጉዳይ ይሆንና አንዳንድ ልጆች ለወላጆቻቸው ሸክም ሆነው የሚኖሩ አይጠፉም። ይህ እንግዲህ መታረም ይገባዋል።

አንድ ጊዜ አንድ እናት በኑሮ ዝቅተኛ የሆኑ ለቤተሰባቸው መተዳደሪያ ቢሆን ብለው የጓሮ አትክልት ይጀምራሉ። አትክልቱም መብቀል እንደ ጀመረ ሴትየዋ ሕመምተኛ ስለ ነበሩና በሽታው ስለ ጠናባቸው (ውኃ ከወንዝ እየቀዱ ነበርና አትክልቱን የሚያጠጡት) መቅዳት ሲያቅታቸው በኋላ አትክልቱ ደረቀ። ለነገሩ እኚህ ሴት አሥር ልጆች ነበሯቸው፣ ግን ምን ያደርጋል ያልዳበረ የሥራ ባህል ያመጣውን ተጽዕኖና ወላጆች ባለ ዕዳ እንደ ሆኑ በመገመት በፉክክር ውኃ ከወንዝ የሚቀዳ ጠፍቶ አትክልቱ ደረቀ። የመሥራት ባህላችሁን አዳብራችኋል ወይ? የመሥራት ልምምድ ከሌለና ፍላጎትን ካላበረታታነው፣ ሥራ ጠላታችን ሊሆንብን ይችላል። በኤፌ. 6÷1-2 ላይ «ልጆች ሆይ፣ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፣ ይህ የሚገባ ነውና» ሲል፣ በቆላ. 3÷20 ላይ «ልጆች ሆይ፣ ይህ ለጌታ ደስ የሚያሰኝ ነውና በሁሉ ለወላጆቻችሁ ታዘዙ»



ይላል።

በመጨረሻም፣ አንድ ነገር ማስታወስ ይገባናል። እናትና አባትን ማክበር የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው። ሙሴ እንደዚህ ብሎ ያስተምር ነበር፡- «እግዚአብሔር አምላክህ እንዳዘዘህ አባትህንና እናትህን አክብር፣ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ላይ እድሜህ እንዲረዝም መልካምም እንዲሆንልህ» (ዘዳግ. 5÷16)። ጳውሎስም በኤፌ. 6÷2-3 ላይ «መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አክብር፣ እርስዋም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት. . . » ይላል። ስለዚህ መታዘዝ በሥራም ቢሆን ጥቅሙ የጋራ ይሆናል፤ የተስፋ ቃልም ይገኝበታል፤ ተስፋውም ይፈጸማል።

በጸሐፊው ቤተሰብ አንድ ልምድ አለ፣ አልጋቸውን የሚያነጥፉትና፣ ክፍላቸውን የሚያስተካክሉት ልጆቻችን ራሳቸው ናቸው። ለወላጆቻቸው ሥራ ሲሠሩ ይከፈላቸዋል። አንድ ጊዜ ሁለተኛው ልጃችን የሥራውን ክብደት በማስረዳት ተከራክሮ የክፍያ ጭማሪ አድርገንለታል። በእኛ እምነት ይህ ለሥራ ፍላጎት መልካም ምሳሌ ይሆናል ብለን እንገምታለን። ሥራ እንዳይንቁ አቅማቸው የሚችለውን ሁሉ ያለማማረጥ እንዲሠሩ እናደርጋቸዋለን። ከመጀመሪያው ጊዜ ይልቅ አሁን ለውጥ እንዳላቸው ተገንዝበን ጥቅም /ዋጋ (ቫሊዩ) ባለማወቅ የሃያ አምስት ሳንቲም ከረሜላ ለመግዛት ብር ይዘው እንደ ሆነ ከረሜላውን ሲያገኙ መልሱን ትተው ይመጡ ነበር። ልጆች ሥራ ይሥሩ ሲባል ከአቅማቸው በላይ እንዳይሆን ወላጆች ጥንቃቄ ልናደርግ ያስፈልጋል። ይህ ጉዳይ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሊታሰብበት ይገባል። ከአቅማቸው በላይ ማሠራት ደግሞ በእድገታቸው ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል ወይም ካደጉ በኋላ ሥራን እንዲጠሉ ያደርጋል።

ትርፍ ጊዜ ሲኖር ሥራን ለመልመድ መሞከር ይጠቅማል። ለምሳሌ፣ «እንጀራ እንዴት ነው የሚጋገረው ብለው ሲጠይቋት፣ እንደ ዳቦ ነው እንዳለችው» እንዳይሆን፣ ሴቶች ልጆችም ከእናቶቻቸው ሙያ ቢማሩ የአገሪቷ ባህል የተጠበቀ ይሆናል፣ እነርሱም የማያሳፍሩ ይሆናሉ። ለምሳሌ፣ በግ በድንገት ለሞት

ዕድሜ ከሚከሠቱት የባሕሪ ለውጦች አንዱ የሆነው የፍትወተ-ሥጋ ፍላጎት ነው። «ጌታ ሆይ፣ ይህንን ፍላጎት ንቀል» ብለው የጾም የጸሎት ፕሮግራም ከያዙ በኋላ ከቦታው ሳይነቀል ሲያገኙት ጌታ ጸሎታቸውን የማይሰማና የማይመልስ ደግሞም የተተዉ የሚመስላቸው ጥቂቶች አይደሉም።

የፍትወተ-ሥጋ ፍላጎት በውስጣችን ያለው ክርስቲያን ስላልሆንን፣ ስላልዳኽን፣ ስላልጾምን ወይም ስላልጸለይን ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በዳኑትና ባልዳኑት ውስጥ ያስቀመጠው ድንቅ ስጦታ ነው። ልዩነቱ ግን እኛ ክርስቲያኖች ይህንን ፍላጎታችንን ማርካት የምንችለው በጋብቻ ውስጥ ብቻ ነው። ስለዚህ ወጣቶች ከዚህ ፍላጎት ጋር የምናደርገውን ትግል በመተው፣ ራሳችንን የጽድቅ ባሪያዎች አድርገን ለእግዚአብሔር እናቅርብ፣ ኃጢአት አይገዛንምና (ሮሜ 6፥12-14)።

ፈተናን ለማሸነፍ ወጣቶች የሚያደርጉት ትግል

እግዚአብሔር ማንንም በክፉ አይፈትንም። በያዕቆብ 1፥14 ላይ፣ «. . . እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል» ይላል። ለፈተና ምክንያት የሆነው ክፉ ምኞት፡- የሥጋ ሥራ፣ የዓለም ንብረትና፣ የሰይጣን መሣሪያ ነው። ስለዚህ እነዚህ ጠላቶቻችን ማለትም ሥጋ፣ ዓለምና ሰይጣን ክፉ ምኞት በማምጣትና በማታለል እኛን የሕይወት ራስ ከሆነው ጌታ ለመለየት ይዋጋሉ። ከዚህም የተነሣ፣ ወጣቶች በፈተና ጸንቶ ለመቆምና ውጊያውን ድል ለማድረግ በተለያዩ ትግሎች ውስጥ ያልፋሉ። ከዚህ በመቀጠል ትግሉን በአሸናፊነት ለመወጣት ወጣቶች ማድረግ የሚገባቸውን ሦስት ነገሮች እንመለከታለን።

ሀ. ሰይጣንን መቃወም፡- ከማንኛውም ክፉ ፈተና በስተጀርባ የሰይጣን እጅ አለበት፣ ሥራውም የተገለጠ ነው። በወጣትነት እድሜያችን ክፉን እንድንመኝ፣ እንድንረክስ፣ ዝሙት እንድንፈጽም፣ ወዘተ. . . ይሸነግለናል። ከዚህም የተነሣ በዘመናችን ብዙዎች በእርሱ ስለ ተሸነገሉ ርኩሰትን፣ መዳራትን፣ ዝሙትን፣ ወዘተ. . . እንደ ዘመናዊነት በመቁጠር በአደባባይ ይለማመዱታል።



ሰይጣን ሰውን የሚሸነግለው በተለያዩ ነገሮች ነው። ለምሳሌ፣ በሚጠፋውና በሚረግፈው ጊዜያዊ በሆነው በዚህ ዓለም ውበት ይጠቀማል። የመሸንገያ ዘዴዎቹም የተለያዩ ናቸው። መዋሸት፣ ማስመሰል፣ ማመቻቸትና ማስገደድ የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል፡ ስለዚህ በአሠራሩና በአሳቡ ላይ ነቅተን ሸንገላውን ልንቃወም ያስፈልጋል። የእግዚአብሔር ቃል፣ «ዲያብሎስን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል» ይላልና። ለመቃወም እንዲቻለን የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ በመልበስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታን ልንሆን ያስፈልጋል (ኤፌ. 6፥18)።

ለ. ዓለምን መካድ፡- ዓለም ያላት ትልቁ ሐብት የሥጋ ምኞት፣ የዓይን አምሮትና ስለ ገንዘብም መመካት ነው። በ1ኛ ዮሐ. 2፥15-16 ያላት ሀብትና ራሷም እንደምታልፍ ወይም እንደምትጠፋ፣ ቀንም እንደ ተቀጠረላት የእግዚአብሔር ቃል ያረጋግጥልናል። እስከዚያ ቀን ድረስ ግን ሰዎችን በተለይ ወጣቶችን ለማታለል ውበት፣ ብልጽግና፣ ብልጭልጭና ለዓይን የሚታዩ ነገሮች ስላሏት ልትማርከን ትሞክራለች።

የእግዚአብሔር ቃል ግን፣ «ማንም ዓለምን ቢወድ፣ የአባት ፍቅር በእርሱ የለም» ይላል። ስለዚህ ዓለምንና በውስጧ ያሉትን ለማሸነፍ የመጀመሪያው እርምጃ እኛ ከዓለም ስላይደለን እርሷን መካድ ነው።

ሐ. ከሥጋዊ ምኞት መሸሽ፡- መጽሐፍ ቅዱሳችን ሰው በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል ይላል። ስለዚህ ምኞት ኃጢአትን እንድንሠራ የመሳብና የማታለል ባሕሪ ስላለው፣ ከክፉ የጎልማሳነት ምኞት ሸሽተን እንድናመልጥ ነው ከጢሞቴዎስ ጋር እኛም የተመከርነው።[25]

## ተጨማሪ ምክር ለወጣቶች፡-

1. ለምታዩት ነገር ጥንቃቄ አድርጉ፤ ለምሳሌ፡- የወሲብ ፊልም /Pornography/ አትመልከቱ። ማቴ.5:28፣ «ሴትን በምኞት ዓይን የተመለከተ ሁሉ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሮአል»፣

[25] ሀብታሙ ከፋር፣ ወጣቶችና የቅድመ- ጋብቻ ሕይወት፣ 1993 ዓ.ም፣ ገጽ 10-11።

በተጨማሪ ዘፍጥ. 3፥6ንም ተመልከቱ:: ኢዮብ 31:1፣ «ወደ ኰረዳዪቱ ላለመመልከት ከዐይኔ ጋር ቃል ኪዳን ገብቻለሁ::»

2. ማግባት የሚገባው እድሜ ላይ ከደረሳችሁና የምትወዷት/ዱት እጮኛ ካላችሁ አግቡ::
3. ከተቃራኒ ጾታ ጋር አግባብ ያለው ኅብረት ይኑራችሁ::
4. ሥራ የፈታ አእምሮ እንዳይኖራችሁ ተጠንቀቁ::
5. ለኃጢአት እምቢ ማለትን ልመዱ (ዘፍጥ. 39፥7-13፤ ዕብ. 11፥24-27)::

## የውይይት ጥያቄዎች

1. የወሲብ ፊልሞችን ማየት ምን አደጋ አለው?
2. በያዕቆብ 1፥14 መሠረት ሰው በፈተና የሚወድቀው እንዴት ነው?
3. በውስጣችን የፍትወተ-ሥጋ ፍላጎት ሲሰማን ምን ማድረግ አለብን?
4. ከላይ ባሉት አምስት ምክሮች ላይ ሌላ አምስት ጨምራችሁ ተነጋገሩ::
5. ከፉ የጎልማሳነት ምኞት ማለት ምን ማለት ነው?

# ሠላሳ አራተኛ ጥያቄ

## በዓይን ፍቅር ተነድፌአለሁና ምን ላድርግ?

በዓይን ፍቅር መነደፍ በጎ ጎን ቢኖረውም፣ አሉታዊ ጎኑ ግን የበዛ ነውና ሊመረመር ይገባዋል:: በጎ ጎኑ ሰው በልቡ የሚወድደው በአብዛኛው በዓይኑ አይቶ ነውና፣ አይቶ መውደድ ተገቢ ነው:: በሌላ ጎኑ ዓይን የውጪውን ብቻ ነውና የሚያየው የተወደደውን ሰው የውስጥ ማንነት ስለማያሳይ ጊዜን፣ መቀራረብንና መታገሥን ይጠይቃልና፣ በዓይን ፍቅር ተነድፌአለሁ በማለት ብቻ ወደ ዘላቂ ግንኙነት ለማምራት ያስቸግራል::

ይህን ዓይነት ፍቅር ተማምኖ ዘላቂ ግንኙነት ለመመሥረት



መነሣት ማለት በአሸዋ ላይ ሕንጻን እንደ ማነጽ ነው:: ይህ እፍላ ፍቅር የጊዜን ፈተና መቋቋም አይችልም:: በቆይታ ውስጥ ትክክለኛ ማንነት ሲገለጽ፣ ወይም የወሲብ እርካታ ሲገኝ፣ እንደ መልአክ ይታይ የነበረው ተፈቃሪ አስጠሊታ ይሆንና ከእርሱ ወይም ከእርሷ ለመለየት መቻኮል ይመጣል:: አምኖን በፍቅሯ ተነድፎ ሲታመም ቆየና የሚፈልጋትን ትዕማርን አግኝቶ ስሜቱን ካረካ በኋላ ፈጽሞ እንደ ጠላት ታሪኩ ሲናገር፣ «አስቀድሞም ከወደዳት ውድ ይልቅ በኋላ የጠላት ጥል በሰጠ» ይላል (2ኛ ሳሙ. 13፥15):: የአምኖን ፍቅር ሥር የሰደደ አልነበረም:: ትዕማርን የፈለገው ለጊዚያዊ የወሲብ ስሜት ማብረጃ እንጂ፣ ከእርሷ ጋር ለዘለቄታው ለመኖር አልነበረም:: ምክንያቱም እርሷ ከተደፈረች በኋላ አብረን ብንኖር ይሻላል ብላ አሳብ ስታቀርብ ሊቀበላት ፈቃደኛ አልነበረም:: እፍላ ፍቅር ስለሚከዳ አያስተማምንም:: ተጋቢዎች በዚህ ፍቅር ተነድተው ትዳር ቢመሠርቱም የኋላ ኋላ ወደ ጸጸትና ተስፋ መቁረጥ ሊገቡ ይችላሉ:: ምክንያቱም ትክክለኛ ምርጫ እንዳላደረጉና የፈለጉትን የትዳር ጓደኛ እንዳላገኙ ማሰብ ይጀምራሉ:: በአእምሮአቸው የሳሉትን የትዳር ጓደኛ ስላላገኙ የጠበቁትን የትዳር ሕይወት መኖር እንደማይችሉ ያስባሉ::

ነገር ግን እፍላ ፍቅርን በአሉታዊ ጎኑ ብቻ ማየቱ አስቸጋሪ ነው:: አንዳንድ ጊዜ በጥንቃቄና በሚገባ ራስን መቆጣጠር በሞላበት የተያዘ የፍቅር ስሜት ግለት ወደ ዘላቂ የጋብቻ ግንኙነት ሊያመራ ይችላል:: የሁለቱ ጓደኛሞች አብሮ መሆን፣ መፈላለግና መርካት፣ በግንኙነታቸው መካከል እርካታና ፍቅር መኖሩን ወደሚያስተውሉበት ደረጃ ይመራቸዋል:: በጥበብ የተያዘ እፍላ የሆነ የዓይን ፍቅር ወደ ዘላቂ ፍቅር ሊሸጋገር ይችላል:: በነፋስ ላይ መከነፍ ብቻ ሳይሆን ዋጋም የሚያስከፍል ሂደት መሆኑን ከተገነዘቡ፣ ፍቅራቸው ሊዘልቅ ይችላል:: ይህ ግን በቀላሉ የሚገኝ ፍሬ አለመሆኑ መታወቅ አለበት::[26]

### የዓይን ፍቅር ሊያመጣ የሚችለው ችግር

1. ተግባርን ያስተጓጉላል::

[26] ከበደ በከሬ፣ ጋብቻን እንዴት ልጀምር? 1995 ዓ.ም፣ ገጽ 51::

2. እውነተኛነቱ አናሳ ነው::

3. እንቅልፍ ያሳጣል::

4. የምግብ ፍላጎት ይቀንሳል::

5. የተወደደው ሰው እንኳን ሳያውቅና ሳይቀበል ይችላል::

6. ያነጫንጫል፣ ወደ ብቸኝነት ሕይወት ይከትታል::

7. ያከሳል፣ «የንጉሥ ልጅ ስለ ምን ከሳህ. . .» (2ኛ ሳሙ. 13:4)::

ስለዚህ፣ ወደ ጥያቄው ስንመለስ፣ የወደዳችሁትን ሰው ቀርባችሁ አነጋግሩ:: ምናልባት ከላይ እንዳየነው ተቃራኒ የሆነ ምላሽ ልታገኙ ስለምትችሉ፣ ራሳችሁን አዘጋጁ:: የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሊረዷችሁ ስለሚችሉ ወደ እነርሱ ሳትፈሩ መቅረብንም ችላ አትበሉት::

## የውይይት ጥያቄዎች

1. በዓይን ፍቅር የተነደፈ ሰው ምን ማድረግ አለበት?
2. የዓይን ፍቅር የሚያስከትላቸው ችግሮች ምንድን ናቸው?
3. የዓይን ፍቅርን በአሉታዊ ጎኑ ብቻ ማየቱ ተገቢ ነውን?
4. አንተ በዓይን ፍቅር ብትነደፍ ምን ማድረግ ትችላለህ?
5. ወላጆች በዓይን ፍቅር ለተነደፉ ልጆቻቸው ምን ማድረግ አለባቸው?

# ሠላሳ አምስተኛ ጥያቄ

## እጮኛ ለመምረጥ
## የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት እውቃለሁ?

ወጣቶች ወደ ፊት የሚመሠርቱት ጋብቻ ክቡር የሆነ፣ የሚደሰቱበትና ለእግዚአብሔር ክብር የሚመሰክሩበት ይሆን ዘንድ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ፈቃድ ለመጀመር ማሰብ፣ በእግዚአብሔርም በሰውም ዘንድ የሚያስደሰት ነውና ይህንን ጥያቄ ማንሣቱ ተገቢ ነው::



«ፈቃዱን በማወቅ ማንን ላግባ?» ለሚለው ጥያቄ የእግዚአብሔር የአምላካችን ቃል በሦስት መንገድ በመክፈል ያስተምራል::

1. የሚያምን ከሚያምን ጋር ይጋባ (2ኛ ቆሮ. 6÷14-15)::
2. የምትወዳትን አግባ (መኃልየ 5÷8)::
3. የሥጋ ዘመድህን አታግባ (ዘሌዋ. 20÷17-21)::

ከላይ እንዳየነው፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነች/የሆነ እጮኛ አግኝተን ለመጋባት የሚረዳን የመጀመሪያው የፈቃዱ ማወቂያ መንገድ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ሮሜ 12÷2 ላይ፣ «የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ» ይላል:: በአጭሩ ይህ ቃል የእግዚአብሔር ፈቃድ:-

- በጎ ነው /ክፋት የለበትም/ (ኤር. 29÷11)፣
- ደስ የሚያሰኝ ነው /አያሳዝንም/፣
- ፍጹም ነው፣ (break) የለበትም ይላል::

እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ትዳር ለመመሥረት ከፈለግን፣ እነዚህን መመሪያዎች ልንከተል ያስፈልጋል::

በአጠቃላይ፣ ወደፊት በትዳር ዓለም ለምንኖረው ሕይወት የዛሬው ምርጫችን መሠረት ስለሆነ፣ ስንመርጥ እንዳንሳሳት ለእግዚአብሔር ቅደሚያ እንስጥ::

### የትዳር ጓደኛን ለመምረጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ

«. . . ነገሩ ከእግዚአብሔር ዘንድ መጥቶአል፤ ክፉም በጎም ልንመልስልህ አንችልም» (ዘፍጥ. 24÷50)::

«ቤትና ባለጠግነት ከአባቶች ዘንድ ይወረሳሉ፤ አስተዋይ ሚስት ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ናት» (ምሳ. 19÷14)::

ብዙዎቻችን በየዕለቱ በምንወስናቸውና በምናሳልፋቸው ጥቃቅን ነገሮች እንኳን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መሆን እንደሚፈልግ

እናስተውልም። ከዚህም የተነሣ ለዚህ ነገር ብጸልይም ባልጸልይም ለእግዚአብሔር ጉዳዩ አይደለም ብለን የራሳችንን እርምጃ እንወስዳለን። በሌላ ጎኑ ደግሞ ፈቃዱን ለማወቅና እርዳታን ለመጠየቅ ወደ እርሱ የምንጮኸው ከአቅማችን በላይ የሆነ ነገር ሲገጥመን ብቻ ነው። የትዳር ጓደኛን ምርጫ በተመለከተ ግን ከማሰብ እስከ ማግባት ድረስ ባለው ሁኔታ ለእግዚአብሔር ዕድል ልንሰጠው ይገባል።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ለምን አስፈለገ?

«. . .አሁንም ከእርሱ ጋር ተስማማ፣ ሰላምም ይኑርህ፤ በዚያም በጎነት ታገኛለህ» (ኢዮ. 22÷21)።

«የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ . . .» (ሮሜ 12÷2)።

ቀደም ሲል እንደ ገለጽኩት፣ በ1ኛ ቆሮ. 7÷39 ላይ፣ «በጌታ ይሁን እንጂ የወደደችውን ልታገባ ነጻነት አላት» በሚለው ቃል መሠረት ክርስቲያን ከሆነች የወደድናትን ልናገባ ነጻነት አለን። ይህንንም ብናደርግ ኃጢአት አይደለም። ነገር ግን ሰላም፣ በጎነት፣ ደስታና ፍጹም የሆነ ነገር የሚገኘው የእግዚአብሔርን ፈቃድ አውቀን ከእርሱ ጋር ተስማምተን በምንመሠርተው ትዳር ውስጥ ነው።

ብዙዎች የትዳርን ዓለም እንደ ተመኙትና እንደ ጠበቁት ሳይሆን የተገላቢጦሽ ሆኖባቸው የሚያማርሩት፣ ዕለት ዕለት በነገሮች ካለመስማማታቸውና ከመጣላታቸው የተነሣ ትዳራቸው የምድር ላይ ሲኦል የሚሆንባቸው፣ አልፎ ተርፎም ለፍቺ ከሚያበቃቸው ምክንያት አንዱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳያስቀድሙ የመሠረቱት ጋብቻ ነው።

እንዲህ ብዬ ስናገር ግን፣ በትዳር ሕይወት ውስጥ ባልና ሚስት አብረው በሚኖሩበት ጊዜ በመካከላቸው ትንሽም ትልቅም ግጭቶች ሲከሰቱ፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን ስለ ተጋቡ ነው ማለቴ አይደለም። አንዳንዶቹ በባሕሪ ልዩነቶች ምክንያት ከሚከሰቱት



ግጭቶች የተነሣ ቀድሞውኑ መጋባታችን የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም እያሉ ያማርራሉ። ይህ ግን ምንም ትርፍ የማያመጣ መረዳት ነው። ከተጋባን በኋላ እግዚአብሔር ትዳራችንን እንዲፈውስ መጸለይ እንጂ ፈቃዱ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ምርመራ ውስጥ መግባት አስፈላጊ አይደለም። ነገር ግን ያላገባን ወጣቶች ወደፊት በትዳር ዓለም ውስጥ ሲገጥሙን በሚችሉ ማናቸውም ዓይነት ችግሮች፣ «የተጋባነው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር በሚሆነው ነገር ሁሉ ዓላማ አለው» ብለን በዓለት ላይ እንደ ተሠራ ቤት ጸንተን ለመቆም እንድንችል፣ ከመጋባታችን በፊት ዛሬ ማንን ማግባት እንዳለብን ፈቃዱን ለይተን እንወቅ።

በክርስቲያናዊ ጋብቻ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ አንድ ቤተሰብ በአንድ አገር ውስጥ ሲመሠረት ለአገሪቱ ሰላም፣ ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ ወዘተ. . . እድገት መሠረት በመሆን ይጠቅማል። በተቃራኒው፣ ከጅማሪያቸው እስከ ፍጻሜያቸው ድረስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከማያስቀድሙ ትዳሮች የተነሣ የጎዳና ተዳዳሪዎች፣ የዝሙት አዳሪዎች መብዛትና የብዙ ታዳጊ ወጣቶች ፀባይ መበላሸት፣ ወዘተ. . . ይከሰታል። ከዚህም የምንረዳው፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማስቀደም ከግል ኑሮ እስከ አገር እድገት ድረስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ነው። የአንድ ጤናማ ኅብረተሰብና ትውልድ መሠረቱ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የተጀመረ ቤተሰብ ነውና።

ስለዚህ ለማግባት የምትፈልግ ወገኔ ሆይ፣ «ታሞ ከመማቀቅ፣ አስቀድሞ መጠንቀቅ» እንደሚባለው፣ እስከ ሕይወትህ ዘመን ፍጻሜ በማይለቅህ ወጥመድ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ተጠምደህ ከምትሠቃይ፣ ዛሬ፣ ፈቃዱን የማወቅ አስፈላጊነትን እንድትረዳና ለማወቅ እንድትተጋ እመከርሃለሁ።

የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዴት ይታወቃል?

«. . . እንተ ጠጣ፣ ግመሎችህን ደግሞ አጠጣለሁ የምትለኝ ቆንጆ፣ እርስዋ ለባሪያህ ለይስሐቅ ያዘጋጀሃት ትሁን፣ በዚህም ለጌታዬ ምሕረትን እንዳደረግህ አውቃለሁ» (ዘፍጥ. 24÷14)።

ከላይ እንዳየነው ለማግባት በሚፈልጉት ልብ ውስጥ የሚመላለሰው ጥያቄ፣ «የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት ማወቅ እችላለሁ?» የሚል በመሆኑ፣ ክዚህ በመቀጠል ጌታ በውስጤ ያስቀመጠውን አሳብ አካፍላለሁ:: አንድ ክርስቲያን ዕለት በዕለት በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ መኖር ወይም የእግዚአብሔርን ፈቃድ አውቆ መመላለስ አለበት እንጂ፣ የትዳር ጓደኛን ለማግኘት ሲፈልግ ብቻ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ የሚሞክር ከሆነ ፈጽሞ ይደነጋገራል::

የእግዚአብሔር ፈቃድ አንዲት ናት:: እርሷንም በሁለት ክፍለን ማየት እንችላለን:: ሁለተኛው በአንደኛው ውስጥ ይጠቃለላልና:-

1ኛ. አጠቃላይ የሆነ ፈቃድ፣

2ኛ. ለግላችን የምንፈልገው ፈቃድ::

1. አጠቃላይ ፈቃድ :- ከዚህ አጠቃላይ ፈቃድ ክርስቲያን ማንን ማግባት እንዳለበት ወይም ጋብቻ መፈጸሚያ ክልሉን ያውቃል:: ስለዚህ ከዚህ ክልል ውጪ የሚደረግ ጋብቻ ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም:: ክዚህ በፊት እንደ ገለጽኩት፣ በዚህ ክልል ውስጥ ፈቃድህ ነውን? ብለን ሳንጠይቅ እንኳን የምንፈጽመው ጋብቻ ኃጢአት ባይሆንም፣ እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን የሚያዘጋጅ አምላክ ስለሆነ ፈቃዱን ሳናረጋግጥ እንደ ፍላጎታችን ወደ ትዳር ዓለም ዘው ብለን መግባት የለብንም::
2. ለግላችን የምንፈልገው ፈቃድ:- እግዚአብሔር አፍ እያላቸው እንደማይናገሩ እንደ አሕዛብ አማልክት አይደለም። አንደበትን ሁሉ የፈጠረው እርሱ ነውና ይናገራል:: እግዚአብሔር ያኔ በገነት አዳም፣ «ይህቺ አጥንት ክአጥንቴ ናት» በማለት ይናገር ዘንድ ሔዋንን ወደ እርሱ እንዳመጣትና የአብርሃምን ሎሌ ደግሞ እንደ መራ፣ ለእኛም እንደዚሁ ያደርግልናል::[27]

በተጨማሪም፣ በህልም፣ በራእይ በትንቢትና በመገለጥ እግዚአብሔር ፈቃዱን ሊገልጥ ይችላል:: ሆኖም ግን፣ እነዚህ

[27] ሀብታሙ ከድር፣ ወጣቶችና የቅድመ -ጋብቻ ሕይወት፣ 1993 ዓ.ም፣ ገጽ 51-53::



ነገሮች በዚህ ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ማደናገርን እያመጡ ስለሆነ፣ በእግዚአብሔር ቃል ሳንመረምርና እርግጠኛ ሳንሆን ዘለን እንዳንገባባቸው ብርቱ ጥንቃቄ ያስፈልጋል::

የሰውን ማንነት ለማወቅ መቅመስ አይቻልም፣ ነገር ግን በቆይታ ባሕሪውን በመጠኑም ቢሆን ማወቅ ይቻላልና ለዚህ እንዲረዳን ስለ ሰው ልጆች ባሕርይ በዘርፉ ያጠኑና የተጠበቡ ምሁራን የደረሱበትን አራት ዓይነት የሰው ልጆችን ባሕሪ በንድፈ አሳብ ደረጃ እንደሚከተለው እንመለከታለን::

**1. ሜላንኮሊ (Melancholy)**

እንደ እነዚህ ያሉ ሰዎች ድብቅ ሰብአዊነት ያላቸው ሲሆኑ፣ ራሳቸውን በራሳቸው የሚደብቁ ዓይነት ናቸው:: እነዚህ ሰዎች ሙዚቀኞች፣ አርቲስቶችና ፈላስፎች ሲሆኑ፣ ራሳቸውን በአንድ ቤት ውስጥ ዘግተው ለብዙ ጊዜ ሊያቆዩ የሚችሉ ናቸው:: ከሰው ጋር ለመኖር ይከብዳቸዋልና፣ ስሜታዊነትም ያጠቃቸዋል:: ስውን ከተቹ ብዙውን ጊዜ ትክክለኞች ሆነው ይገኛሉ፣ አስተዋዮች ናቸውና:: ሜላንኮሊ (Melancholy) ፊታቸው በቀላሉ የማይፈታ፣ ኮስታራና ሁል ጊዜ ትክክለኛ መሆንን የሚፈልጉ፣ በቀላሉ የሚጎዳ ስሜታዊ ተፈጥሮ ያላቸውና አኩራፊ ቢጤ ናቸው::

**2. ፍሌግማቲክ (Phlegmatic)**

እነዚህ ድብቅ እኔነት ያላቸው ሲሆኑ፣ በመጠኑ ደስተኞች ናቸው ይባላል:: ንጹሕ ነገር የሚወዱና ጥሩ ዲፕሎማቶችም ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው:: ጠዋት ጠዋት ከእንቅልፋቸው የሚነሡት በግድ ነው:: የሂሳብ ሠራተኞችና ቴክኒሺያኖች ይበዙበታል:: ባሕሪያቸው ብዙ አይለዋወጥም፣ ለሰው መልካም አመለካከት ያላቸውና ታማኞችም ናቸው:: ብዙ ቀልድ አይሆንላቸውም፤ ብቸኞች ናቸው:: በጣም ራሳቸውን ስለሚወዱ ውሳኔ ለመስጠት

ይዘገያሉ፣ ያምጣሉም። ዝምተኛ፣ ዝግተኛ፣ በቀላሉ የሚወሰዱ፣ ሚዛናዊ ባሕርይ ያላቸው፣ በቀላሉ የማይናደዱና የማይሰቁ ዲፕሎማት ናቸው።

**3. ኮለሪክ (Choleric)**

ባሕሪያቸው በግልጽ ይታወቃል። አምራቾች ናቸው። መሪዎችና ፖሊሶች እንዲሁም ግንበኞች ይበዙባቸዋል። የቁርጥ ቀን ልጆች ናቸው ማለት ይቻላል። ራእይ ያላቸውና ተስፋ የማይቆርጡ ናቸው። ስሜታቸውን ግን ብዙ መግለጽ አይወዱም። ለምሳሌ፦ ሚስታቸውን «እወድሻለሁ» ማለት እንኳን አይሆንላቸውም።

**4. ሳንጉዊን (Sanguine)**

እነዚህ ግልጽ ናቸው። ፈገግታ አይለያቸውም። ተግባቢና ጥሩ የሽያጭ ሠራተኞች ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው። በአብዛኛው ባልንጀራ አያጡም። ዝርክርክነት ያጠቃቸዋል። የደመወዝ አካባቢ አያሌ ወዳጆች አሏቸው። ተናጋሪዎችና የመድረክ ሰዎችም ናቸው። ደስተኛ፣ ፍልቅልቅ፣ ሁሉን ለማስደሰት የሚፈልጉ፣ ድራማ - ነክ ዓይነት ባሕሪ ያላቸው ተግባቢና ስሜታዊ፣ ወዘተ . . . ሲሆኑ፣ ችግር ሲገጥማቸው በትንሹ ይከፋሉ፣ አይቋቋሙትም። እንደ ካንዴላ የእሳት ብልጭታ ፈጣሪዎች ናቸው።»[38]

## የውይይት ጥያቄዎች

1. ወጣቶች እጮኛ ለመምረጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት ማወቅ ይችላሉ?
2. ሰዎች ትዳር ለመያዝ እንዲችሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ያለባቸው ሦስቱ መንገዶች ምንድን ናቸው?

[38] ተሾመ ነጋሽ፣ <u>እንዴህ ቢሆን ኖሮ</u>፣ 1997 ዓ.ም፣ ገጽ 97።



3. በሮሜ 12:2 የእግዚአብሔር ፈቃድ የምናውቅባቸው ምልክቶች የትኞቹ ናቸው?
4. ትዳርን አስመልክቶ እግዚአብሔር በሕልምና በራእይ ፈቃዱን ሊገልጽ ይችላል? እንዴት?
5. አራቱን ዓይነት የሰው ባሕሪ ደረጃዎች አውጣና የአንተን ለይተህ እወቅ።

# ሠላሳ ስድስተኛ ጥያቄ

## ሳላገባ መኖር እፈልጋለሁና ምን ላድርግ?

እግዚአብሔር በቃሉ ላይ ሰው ሁሉ እንዲያገባ ፈቅዷል። «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም. . .» (ዘፍጥ. 2÷18)። ነገር ግን እንዳያገባ ደግሞ ከፈለገ እንዲያገባ የፈቀደው እርሱ እንዳያገባ ደግሞ ፈቃድ መስጠት አለበት እንጂ፣ በሰው አላገባም በሚል ፍላጎት ሊሆን አይችልም። እስቲ ወደዚህ ጥያቄ ምላሽ ከመምጣታችን በፊት፣ ሰዎች ለምን እንደማያገቡ ምክንያታቸውን እንመልከት፡-

1. የሚስማማቸውን የትዳር ጓደኛ ስላላገኙ።
2. የተሳሳተ ሃይማኖታዊ አመለካከት ስላላቸው፣ «የእኔ ትዳሬ ጌታ ብቻ ነው» የሚል ማለት ነው።
3. ከጋብቻ በኋላ ያለውን ሕይወት በሩቁ በመፍራት።
4. ጋብቻን እንደ መታሰር በመቁጠር።
5. እጮኛ ለመጠየቅ ስለሚፈሩ።
6. ከዚህ ቀደም በፍቅረኛቸው ተከድተው ከሆነ።
7. በአእምሮአቸውና በአካላቸው ብቃት ከሌላቸው
8. የግብረ-ሰዶማዊነት ዝንባሌ /ልምምድ/ ካላቸው።
9. በኢኮኖሚ ችግር ያለባቸው ከሆነ።
10. ከጋብቻ ውጪ የወሲብ ሕይወትን የሚለማመዱ ከሆነ።

ሳያገቡ ለመኖር ከላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች በቂ አይደሉም። ምክንያቱም በእግዚአብሔር የታመነ ሰው እግዚአብሔር ከእነዚህ ምክንያቶች በላይ እንደ ሆነና እንደሚያስተካክላቸው ያውቃልና።

ይህን ጥያቄ የጠየቃችሁ ወገኖቼና አሁን ይህንን መጽሐፍ እያነበባችሁ ያላችሁ ሁሉ፣ እናንተ ላለማግባት የምታቀርቡት ምክንያት የትኛው ይሆን? እግዚአብሔር ታማኝ ነውና በእርሱ ታመኑ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሦስት ምክንያቶች እንዳያገቡ የተከለከሉ ሰዎች አሉ (ማቴ. 19፥10-12):-

1. ከእናቱ ማኅጸን ጀምሮ ጃንደረባ የሆነ (የወንድ ብልት የሌለው)።
2. በሰዎች ጃንደረባ የሆነ (ብልቱ ከሥሩ የተቆረጠበት ወይም «የተሰለበ»)።
3. እራሱን ለመንግሥተ ሰማያት ጃንደረባ ያደረገ (ሙሉ አካል እያለው)።

ከላይ ከ፲-2 የተጠቀሱት ሰዎች ምንም እንኳን የጾታ አካል ባይኖራቸውም፣ የወሲብ ፍላጎት ግን አላቸው። ሦስተኛው ላይ የተጠቀሰው ሰው ግን የጾታ አካል አለው፣ የወሲብ ፍላጎቱ ግን ለእግዚአብሔር ተሰጥቷል። ይህንም ያደረገው ሰውየው ሳይሆን አራሱ እግዚአብሔር ነውና አስችሎታል። ስለዚህ ከላይ ከተጠቀሱት ሦስት ምክንያቶች ውጪ የሆነ ሰው ሁሉ እንዲያገባ ተፈቅዶለታልና ለጋብቻ ተዘጋጁ።

## የውይይት ጥያቄዎች

1. ሳያገቡ መኖር ለሚፈልጉ ሰዎች የአንተ ምክር ምንድን ነው?
2. ከ1-10 ካሉት ምክንያቶች ውስጥ አንተ የተቸገርክባቸው ምክያቶች የትኞቹ ናቸው? ለምን?
3. ሰው ከጋብቻ ነፃ የሚሆንባቸውን መንገዶች በመዘርዘር ተወያዩ።
4. የወሲብ ፍላጎት ኖሯቸው የጾታ አካል የሌላቸው ሰዎች ፍላጎታቸውን ለማርካት ምን ያድርጉ?
5. በራስ አነሣሽነት ብቻ ራስን ለመንግሥተ ሰማይ ስልቦ መኖር ይቻላል? ለምን?



## ሠላሳ ሰባተኛ ጥያቄ

## በእጮኝነት ጊዜ መሳሳም (Kissing) ኃጢአት ነው?

መሳሳም ኃጢአት የሚሆነው መዳራት ሲታከልበት ነው። የጥያቄውም መንፈስ ይኸው ይመስለኛል። ብዙ ወጣቶች በእጮኝነት ላይ ብዙ ጥያቄ ያነሣሉ። «ፍቅራችንን እንዴት ነው የምንገላለጸው? ከንፈር ለከንፈር ካልተሳሳምንና ሰውነታችንን ካልተደባበስን፣ እንግዳ ሆነን መኖራችን አይደለም ወይ?» ይላሉ። መሳሳም ኃጢአት ነው ወይስ አይደለም ወደሚለው ድምዳሜ ከመድረሳችን በፊት፣ የምናደርገውን ነገር ሁሉ እንደ ክርስቲያን ከእኛ ጥቅም አንጻር ብቻ ሳይሆን ለእግዚአብሔርስ ምን ክብር ያመጣል ብለን መጠየቅ አለብን። ቃሉ «. . . . ማናቸውን ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት» (1ኛ ቆሮ. 10፥31) ይላልና። የእጮኝነት ጊዜ ማለት በተቀደሰ አኗኗርና በፈሪሃ እግዚአብሔር ሕይወት ወደ ጋብቻ የምንጓዝበት መንገድ ነው እንጂ በፈለግን ጊዜ የምንተወው የከንፈር ወዳጅነት ጊዜ አይደለም።

መተጫጨት አለማውያን «የከንፈር ወዳጅነት» እንደሚሉት አይደለም።

በከተማ አካባቢ ያሉ ወጣቶች ዘመናዊነት አየመሰላቸው የከንፈር ወዳጅነት ሲመሠርቱ ይስተዋላሉ። በዚህም የተነሣ እከሲት «ገርል ፍሬንዱ ናት»፣ «እከሌ እኮ ቦይ ፍሬንዷ ነው» ሲሉ ይደመጣሉ። አባባላቸው የሚገልጸው በወጣትነት ዕድሜ ከብዙ ሰዎች ጋር ከመነካካት አንድ ለአንድ መሆን ይሻላል፤ ይኸውም ከተሣካ ለመጋባት፣ ካልሆነ ግን ለጊዜው እርስ በርስ ለመጠቃቀም ከመረጡት ሰው ጋር ነው። ይህ አሳብና ተግባር ግን የጨለማው ዓለም ገዢ ካሳወረው አእምሮ የመነጨ እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም።

ወጣቶች በእንግሊዘኛው «ፋየር ኤጅ» በሚባለው የእድሜ ክልል ውስጥ ሰላሉ፣ ከእድሜያቸው ጋር የተያያዙ ብዙ የሚያስቸግሯቸው ነገሮች አሉ። ቢሆንም የሴት ወይም የወንድ ጓደኛን በመያዝ የተሰማንን ፍላጎት፣ ጾታዊ ግንኙነትንም ጨምሮ፣ ማግኘት መፍትሔ አይደለም። ምክንያቱም ከከፉ የጎልማሳነት ምኞት ማምለጥ የምንችለው እንደ እግዚአብሔር ቃል «በመሸሽ» እንጂ የፍላጎታችንን ማርኪያ በመፈለግ አይደለም። እግዚአብሔርም ቢሆን ከምንችለው በላይ ከእኛ አይፈልግም። በመንፈስ ቅዱስና በጸጋው ብርታት ወጣትነትን በድል መሻገር የማንችል ብንሆን ኖሮ፣ እግዚአብሔር እኛን በወንጌል ባልጠራን ነበር።

ስለዚህ ወጣት ወንዶችና ሴቶች ዘለቄታ ለሌለውና ለብዙ ችግር ለሚያጋልጠው ርካሽ ዓላማ ማለትም ከንፈር ወዳጅነት ራሳችሁን ልትሰጡ አይገባም።

*ለመሆኑ መተጫጨት ከላጤነትና ከመጋባት ልዩነት አለውን?*

የእግዚአብሔር ቃል ማጨትን ከላጤነት ሲለይ፣ «ማናቸውም ሰው ድንግልና ያላትን ልጃገረድ ቢያጭ፣ ሌላ ሰውም በከተማ ውስጥ አግኝቶ ከእርስዋ ጋር ቢተኛ፣ ሁለቱንም ወደዚያች ከተማ በር አውጡአቸው. . . እስኪሞቱ ድረስ በድንጋይ ውገሩአቸው. . . » ሲል፣ በሌላ ቦታ ደግሞ፣ «ማናቸውም ሰው ድንግልና ያላትን ያልታጨች ልጃገረድ ቢያገኝ፣ ወስዶም ቢደርስባት ቢያገኙትም፣ . . . ሚስት ትሁነው፣. . .» በማለት ይገልጻል (ዘዳግ. 22፥23፣28-29)።

ምንም እንኳን መተጫጨት ወደፊት ከማን ጋር እንደምንኖር እንድናውቅ በማድረጉ ከላጤነት የሚለይ ቢሆንም፣ ከመጋባት ጋር ግን አንድ አይደለም።[29]

ፍቅራችሁን የምትገልጹባቸው ሌሎች ጤናማና የእግዚአብሔርን ስም የማያስነቅፉ መንገዶች መፈለግ ይኖርባችኋል። በእጮኝነት ጊዜ ማድረግ ያለባችሁ፣ ከጋብቻ በፊት ማድረግ ያለባችሁን እንጂ፣ ከጋብቻ በኋላ ማድረግ ያለባችሁን

[29] ሀብታሙ ከድር፣ ወጣቶችና የቅድመ ጋብቻ ሕይወት፣ 1993 ዓ.ም፣ ገጽ፣ 63።



አይደለም። መሳሳም (deep kissing) ከጋብቻ በኋላ የሚደረግ ነው። የቆመን መኪና በዜሮ ማርሽ እንጂ በአምስተኛ ማርሽ ለማስነሣት አትሞክሩ፣ ትቸገራላችሁ። እስኪ በእጮኝነት ጊዜ እንዴት መሳሳም እንዳለባችሁ ይረዳችሁ ዘንድ ዋልተር ትሮቢሽ የተባሉ የጋብቻ አማካሪ ፍራንሷ የተባለ ወጣት ለጠየቃቸው ጥያቄ የሰጡትን ምላሽ (ምክር) ተመልከቱ።

በቅርብ ጊዜ ሽርሽር በምንሄድበት ስፍራ በሚገኘው ለምለም መስክ ላይ ተንጋልላ ተኝታ ሰማይ ሰማዩን ስትመለከት ነበር። መቼም መስኩ ላይ የተኛችው ሰውነቷን ጣል አድርጋ ነበር። ቀሚሷ ያጎጠጎጡ ጡቶቿን ግጥም አድርጎ ይዟል። ለሰላሳው ሰውነቷ እስከ ጭንቅ ድረስ ተጋልጧል። በዚያን ጊዜ ምንም ትዕግሥት ሊኖረኝ አልቻለም። እንዳበደ ሰው ዘልዬ እቅፍ አደረግኳት። እርሷም ከእጄ አምልጣ ብስክሌቶቻችን ወደ ቆሙበት ስፍራ ሮጠች። ከዚያ በኋላ አንድ ቃል ሳንለዋወጥ እኅቷ ቤት ደረስን። በነጋታውም ነገሩን አላነሣነውም።

እንደዚህ ባለ ሁኔታ እስከ መቼ መቃጠል ይቻላል? እስከ መቼስ በስሜት ተራርቀን ስመኖር እንችላለን? አንድ የተጨበጠ ተስፋ ቢኖረን እንኳ ግድ የለም ነበር። ነገር ግን የዛሬ አራት ዓመት ወይም አምስት ዓመት ወይም እስከነ አካቴውም የምንጋባ መሆናችንን ለማወቅ የምንችልበት ዘዴ የለንም።

ተነሥተን እንኮብልል ይሆን? ወዴት ይደረሳል?

የተወደድክ ፍራንሷ፣

እውነተኛ ክርስቲያን እስከ መጨረሻው ይታገሣል፣ እስከ መጨረሻም ተስፋ ያደርጋል። ይህን ከአንድ ወዳጄ የተቀበልኩትን ጠቃሚ ምክር ለአንተ አሳልፌ መስጠት ደስ ይለኛል። ከእንግዲህ ወዲህ ከአንተ የሚፈለገው በሥጋ የምትዋሃዱበትን ዕለት በትዕግሥት መጠበቅ ነው። «የቸኮለ አፍስሶ ለቀመ»፣ እንደሚባለው ሁሉ፣ አጉል ችኮላ አያሻም። በእኔ ግምት በችኮላ የምትፈጽመው ተግባር የነጻነትንና የደስታን ውበት የሚያሳጣ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም።

ከሁሉ አስቀድሜ ነጻነትን ያሳጣል ያልኩበትን ምክንያት ላስረዳህ።

በቃል ኪዳን ቀለበት ተሳስረው የሚኖሩ አንድ ጉብልና ልጃገረድ ነበሩ። ሁለቱ ወጣቶች ከልብ የሚፋቀሩ መሆናቸውን ከማወቃቸውም በላይ፣ በውስጣዊ ስሜታቸው ራሳቸውን እንደ ባልና ሚስት አድርገው ይቆጥሩ ነበር። ረዘም ላለ ጊዜ ተጫጭተው ከቆዩ በኋላ ግን፣ ይሳካል ብለው ያሰቡት የወደፊት ትዳራቸው ግን ሳንካ ያለበት መሆኑን እየተረዱት መሄድ ጀመሩ። በመጨረሻው፣ የገጠማቸውን ችግር ፍርጥርጥ አድርገው ከተነጋገሩበት በኋላ፣ በሰላም ለመለያየት ቻሉ።

እነዚህ ሁለት ወጣቶች ከጋብቻቸው ቀን በፊት በግብረ-ሥጋ ተገናኝተው ቢሆን ኖሮ፣ አብሮ መኖራቸው የማያዋጣ መሆኑን ተረድተው በሚለያዩበት ጊዜ መቼም የማይሽር የጸጸት ጠባሳ ባተረፉ ነበር። ለሲሴል ያለህ ስሜት በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ለተገናኘሃት ልጅ ከነበረህ ስሜት የላቀና የጠለቀ መሆኑን ደህና አድርጌ አውቃለሁ። እኔም እስከ መጨረሻው እንድትታገሥ የምመክርህ፣ ሲሴልን ከልብህ የምትወዳት መሆንህን ስለማውቅ ነው። ስለዚህ ይህን የመሰለው የጠለቀ ፍቅራችሁ በአንድ ባልታሰበ ምክንያት የማያዛልቅ መሆኑ ቢታወቅ እንኳን ቂምና ጸጸት እንዳያተርፍ መጠንቀቅ አለባችሁ።

ብዙ ዓመት ትዳር ይዘው የኖሩ ወንዶች ሚስቶቻቸውን፣ «አንቺን ሳገባ አጉል ስሕተት ማድረጌን ከጋብቻችን በፊት ተረድቼዋለሁ። ማንኛውንም ነገር ሆዴ እያወቀ የሆነ ይሁን በማለት የገባሁበት በመሆኑ፣ የስሕተቴን ዋጋ መክፈል አለብኝ እያሉ» ሲነዘንዟቸው ሰምቻለሁ።

ለሲሴል ያለህ ፍቅር እውነተኛና የማይገታ መሆኑን ከደብዳቤህ በመረዳቴ ደስ ብሎኛል። ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ ጊዜ ስሜት አሳሳች መሆኑን አትዘንጋ። ስሜታችን ዘላቂ መሆኑን ለማረጋገጥ ረጅም ጊዜ መታገሥ ያስፈልገናል። በቅርብ ጊዜ በአሜሪካ የተደረገ አንድ ጥናት፣ በጋብቻቸው ተደስተው የሚኖሩት አብዛኞዎቹ ባለ ትዳሮች ከጋብቻቸው በፊት ለረጅም ጊዜ ተጫጭተው የቆዩ



መሆናቸውን ያረጋግጣል።

የሕክምና ምርመራ ተላካ ለማለት የሚቻለው የተጠረጠረው ሕመም አለመኖሩ ሲረጋገጥ ነው። የመተጫጨት ጊዜም በዚሁ ሊመሰል ይችላል። ከተጫጩ በኋላ መለያየት የማይገባ መሆኑን ማንኛውም ሰው አይስተውም። ይሁን እንጂ፣ በሰላም አብሮ ለመኖር የማያስችሉ እክሎች መኖራቸውን በቃል ማሰሪያና በጋብቻ መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ መርምሮ ማረጋገጥ፣ ሁኔታው የማያዋጣ ሆኖ ሲገኝ፣ በስምምነት መለያየት ተጋብቶ ከመፋታት ይሻላል።

የመተጫጨትን ትርጉም በበለጠ ለማብራራት ከዚህ ቀደም ያቀረብኩልህን የሕፃን ልደት ምሳሌ እንደ ገና ልጠቅስልህ እወዳለሁ። ጋብቻን የመወለጃው ጊዜ በደረሰ ሕፃን ብንመስለው፣ መተጫጨት ደግሞ ጽንሱ በእናቱ ማኅጸን ውስጥ በሚያሳልፈው ጊዜ ሊመሰል ይችላል። በምሳሌው መሠረት የመተጫጨት ቃል ኪዳን ማፍረስ በእናቱ ማኅጸን ውስጥ መረጋጋት ያቃተውን ጽንስ እንደ ማስወረድ ይቆጠራል። በመተጫጨትና በጋብቻ መካከል ወጣቶች የትዳራቸው ዕቅድ በማንኛውም ዓይነት እክል እንዲጨነግፍ ማድረግ አይችሉም። በግብረ-ሥጋ ከተገናኙ በኋላ የቀለበትን ቃል ኪዳን ማፍረስ የተወለደውን ሕፃን አንቆ እንደ መግደል ይቆጠራል።

እንግዲህ ነጻነት ያሳጣል ያልኩት ስለዚህ ነው። ከዚህም በቀር፣ ለግብረ-ሥጋ ግንኙነት መጣደፍ ከእድገት፣ ከብስለትና ከመቆየት የሚገኘውን ደስታ ያበላሸዋል። ከጋብቻ በፊት ግብረ-ሥጋን መፈጸም የሚሹ ሁሉ፣ ወላጆቹ ለልደት የገዙለትን ስጦታ በዓሉ ከመድረሱ ከሁለት ቀን በፊት ተጣድፎ የከፈተውን ልጅ ይመስላሉ ለማለት ይቻላል። ይኸው ሁኔታ የደረሰባት አንዲት በትዳር ላይ ያለች ሴት የሰጠችው አስተያየት ትዝ ይለኛል። ሴትየዋ፣ «እኔና ባሌ ተጫጭተን ለጥቂት ጊዜ በደስታ እንኖር ነበር። በኋላ ግን ሳላስበው እርግዝና ተገኘሁ። ከዚህም የተነሣ ለሠርጋችን ያቀድነውን ዕቅድ መለወጥ ግድ ሆነብን። ጋብቻችንም ያለ ወግና ማዕረግ በጥድፊያ ተከናውኖ በትዳር መኖር ጀመርን። ሁኔታውን ወደ ኋላ

ዘወር ብዬ ስመለከተው በጣም ያሳዝነኛል» ብላለች:: የአንዲት ሴት እለቀናኗ መውሰድ ለሕፃኑ ሕይወት የሚያሰጋ መሆኑ ግልጽ ነው:: እርግጥ ነው ያለቀናቸው ተወልደው የሚያድጉ ልጆች አሉ:: ነገር ግን እንዲህ ያሉት ሕፃናት ብዙ ጉድለትና ችግር ያለባቸው መሆኑ ደግሞ አይካድም::

ፍላጎትህ ገንፍሎ ሲሴልን ዘልለህ ባቀፍካት ጊዜ እጅህን ምንጭቅ አድርጋ የሸሸችው ሆነ ብላ ሳይሆን፣ ክብሯንና ንጽሕናዋን ለመጠበቅ ከተፈጥሮ ባገኘችው ስሜት መሆኑ ግልጽ ነው:: ይህን የመሰለውን እርምጃ ያለ ጊዜው መውሰድ ከደስታው ይልቅ ጸጸቱ የሚያመዝን መሆኑ ሳይሰማት አልቀረም:: የዚያን ዕለት ያደረግከው ሙከራ እንኳን በመካከላችሁ የነበረውን የመንፈስ ኅብረት አቃውሶ ለአንድ ቀንም ቢሆን ወደ መኮራረፍ አድርሷችኋል::

ፍላጎቱን ገትቼ ዝም ያልኳት እንደ ሆነ፣ የምወዳት መሆኔን ወደ መጠራጠር ትደርሳለች ብለህ ያቀረብከውን አሳብ አልቀበለውም:: ይልቁንም፣ ራስህን ለመግታት የምትችል መሆንህን እየተረዳች ስትሄድ፣ ለአንተ ያላት ፍቅር እያደገ እንጂ እየቀነሰ እንደማይሄድ እርግጠኛ ነኝ:: ለጊዜው የሁለታችሁ አብሮ መኖር በድብቅ እንዳለ ነገር ይቆጠራል:: በአሁኑ ሁኔታችሁ ራሳችሁንም ሆነ ውስጣችሁን በሙሉ አልተገላለጣችሁም:: ይሁን እንጂ፣ በሠርጋችሁ ዕለት ልታውቁትና ልትረዱት ተስፋ የምታደርጉት አንድ ድብቅ ነገር እንዲኖር ያሻል:: አለበለዚያ፣ «በእጅ የያዙት ወርቅ ከመዳብ እኩል ነው» እንደተባለው እንዳይሆን ያስፈራል::

ከጋብቻ መሠረታዊ አቋሞች አንዱ የግብረ-ሥጋ ጉዳይ መሆኑ ሁላችንም የምናውቀው ነገር ነው:: ከዚህም በቀር ብልትህ ደካማ አለመሆኑን ታውቃለህ:: ሲሴልም ወንድነትህን የምትጠራጠር አይመስለኝም:: ብልቴ ግብረ-ሥጋ ለመፈጸም አይችልም የሚል ጥርጣሬ ካለህ በሕክምና ምርመራ ጉድለቱን ማረጋገጥና ማስተካከል ይቻላል:: ስለዚህ እኔ የምመክርህ ሲሴልን የሚያስቀይምና ደስታችሁን የሚያደፈርስ እርምጃ ተጣድፈህ እንዳትወስድ ነው::[30]



በእጮኝነት ጊዜ ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባርን በጠበቀ ሁኔታ መመላለስ እንዲችሉ የሚጠቁሟችሁን እነዚህን ነጥቦች ተመልከቱ፡-

1. ስውር ቦታ ውስጥ ብቻችሁን አታሳልፉ (ለፈተና ያጋልጣልና)::
2. አካላችሁን ገልጣችሁ አትሰጣጡ (ጊዜው ገና ነውና)::
3. አወድሻለሁ፣ አወድሃለሁ ተባባሉ (ፍቅርን ያዳብራልና)::
4. የወሲብ ፍላጎት የሚያነሣሱ ፊልሞችን አትመልከቱ (ወደ ተግባር ይገፋፋሉና)::
5. በግልጽ ቦታ አብራችሁ ጸልዩ (የቆይታ ጊዜያችሁም የተወሰነ ይሁን)::
6. መተጫጨታችሁንና መስማማታችሁን ድብቅ አታድርጉት (በድብቅ ለመፍረስ ምክንያት እንዳይሆን)::
7. የእጮኝነታችሁን ጊዜ አታስረዝሙት (ከጊዜ ብዛት የሚነፍስ ነፋስ ይገባልና)::
8. ራሳችሁን የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ (ሮሜ 6÷12-14)፣ ጠላትን ታሸንፋላችሁና::

እንግዲህ፣ በአጠቃላይ፣ በእጮኝነት ጊዜ ስትቆዩ፣ ከዝሙትና ከመዳራት በመራቅ (ዘጸአ. 20÷14፤ገላ. 5÷19)፣ በሰዎቹ ሁሉ ፊት መልካም ምሳሌ በመሆን (1ኛ ጢሞ. 4÷11-12) ልትመላለሱ ያስፈልጋል:: በሠላሳ ሰባተኛው ዓይነት ጥያቄ ለምትቸገሩ ወጣቶች፣ እስከ ሠርጋችሁ ቀን ድረስ በቅዱሳን አሳሳም እየተሳሳማችሁ እንድትቆዩ እመክራለሁ::

## የውይይት ጥያቄዎች

1. በእጮኝነት ጊዜ መሳሳም (Kissing) ኃጢአት የሚሆነው እንዴት ነው?
2. ክርስቲያን ወጣቶች የከንፈር ወዳጅ ሊይዙ ይችላሉ?

---

[30] ዋልተር ትሮቢሽ፣ አንድ ወጣት ወደደ፣ 1995 ዓ.ም፣ ገጽ 92-96::

3. በእጮኝነት ጊዜ ከፍቅረኛህ ጋር ፍቅርህን በአግባቡ እንዴት ነው መግለጥ የምትችለው?

4. የእጮኝነት ጊዜ ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ አስረዳ።

5. መልካም የእጮኝነት ጊዜ ለማሳለፍ ከእጮኛሞች ምን ይጠበቃል?

# ሠላሳ ስምንተኛ ጥያቄ

## ከዕድሜዬ መግፋት የተነሣ ሳላገባ እንዳልቀር ፈርቻለሁና ምን ባደርግ ይሻላል?

ይህ ጥያቄ በመሠረቱ በጣም አስፈላጊ ጥያቄ ነው። ይህንን ጥያቄ እኔ ደግሞ በተመሳሳይ ጥያቄ ለመመለስ እሞክራለሁ። ለምንድን ነው ሰዎች ሳያገቡ ዕድሜያቸው የሚገፋው? ምክንያቶቹ ብዙ ቢሆኑም፣ ጥቂቶቹን እንደሚከተለው እንመልከት።

1. ለትምህርት፣ ለሥራና ለሌሎች ጉዳዮች ብቻ ትኩረት በመስጠት ሊሆን ይችላል። ትምህርቴን ልጨርስና ዲግሪዬን ልያዝ፣ የሙያ ትምህርቴን ልጨርስና ሥራዬን ላሻሽል፣ ጥሩ ለሰው ሲያሳዩት የሚያኮራ ቤት ልሥራ፣ ንብረት ላጠራቅም፣ ወዘተ . . . ። እነዚህን ለመፈጸም ወደ ፊት ደፋ ቀና ስንል፣ ሌት ተቀን ዕድሜያችን ይገፋል። መሃል ላይ ቆም ስንል ማርጀታችን ይታወቀንና ስንነቃ ተስፋ በመቁረጥ ያልሆነ አማራጭ ውስጥ እንገባለን። ስለዚህ ሁሉንም ሚዛኑን በጠበቀ ሁኔታ እያደረግን፣ ማግባት በሚገባን ዕድሜ ልናገባ ያስፈልጋል።

2. የትዳር ጓደኛ መመዘኛችን የማይደረስበት /እንከን የለሽ/ ይሆንና ሁሉንም በምርጫችን እየጣልን እንከን የለሽ ሲጠፋ፣ እንከን የበዛበት ላይ እንወድቃለን። እንከን የሌለው ክርስቶስ ነውና የምርጫ መመዘኛችንን እናስተካክል።

ወንዶች ብቻ ሳይሆኑ ሴቶችም የራሳቸው የትዳር ጓደኛ መምረጫ መስፈርቶች አሏቸው። በአብዛኛው ለማግባት የሚፈልጉትን ወንድ ደፍረው ባይጠይቁም፣ ለትዳር



የሚጠይቃቸውን ሰው የሚመርጡበት መስፈርት ይኖራቸዋል። የሚጠይቃቸው ወንድ የእነርሱን መስፈርት የማያሟላ ከሆነ «እምቢ» ይላሉ። በመስፈርታቸው መሠረት የሚጠይቃቸው ወንድ ካልመጣና ጠብቀው ተስፋ ከቆረጡ ደግሞ፣ ትዳር ለመመሥረት ብቻ ብለው በመጨረሻ የደረሰላቸውን ወንድ ያገባሉ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከተወሰነ እድሜ በኋላ ቀድሞ የተዉትንም አያገኙም። ምቹው ጊዜ ሲያልፍባቸው ደግሞ ቀስ በቀስ የላጤነትን ኑሮ መቀበል ይጀምራሉ።

ማርታ 34 ዓመቷ ነው። በጸሐፊነት ሙያ ከኮሌጅ ተመርቃ ሥራ ከያዘች አሥር ዓመት ሆኗታል። ለማግባት ብትፈልግም፣ ለሚጠይቋት ወንዶች ሁሉ ፈቃደኛ አልነበረችም። እርሷ ማግባት የምትፈልገው ሃብታም የሆነ ነጋዴን ነበር። ነገር ግን አንድም ነጋዴ አልጠየቃትም። እርሷን የጠየቋት ሁሉ አሁን አግብተው ትዳር መሥርተዋል። ይህን ስታይ በጣም ተሰማትና ከእንግዲህ ወዲያስ የመጣልኝን «እንቢ» አልለውም ከሚል ውሳኔ ላይ ደረሰች። ነገር ግን አንድም ሰው ብቅ አላለም። ከዚያም፣ «ወይኔ ቆሜ መቅረቴ» ነው በማለት መጨነቅ ጀመረች። ከዚህ በፊት ጠይቀዋት ፈቃደኛ ያልሆነችላቸውን ወንዶች እያሰበች መቆጨትና ማሰብ ጀመረች። አንድ ቀን በአውቶቡስ ወደ ቤቷ ስትሄድ፣ ከአንድ ወጣት ጋር ትተዋወቃለች። ወጣቱ ልጅ ክርስቲያን አልነበረም። ከዚያ ስለ ጌታ ትነግረውና በሌላ ቀን ይዛው ወደ ቤተ ክርስቲያን ትሄዳለች፣ ወጣቱ ጌታን ይቀበላል። ተከታታይ ትምህርትም መማር ይጀምራል። የወጣቱና የማርታ ግንኙነት እያደገ ሲመጣ፣ ወጣቱ ሊያገባት እንደሚያስብ ነገራት። የወጣቱ ዕድሜ 28 ዓመት፣ ሥራ የሌለውና ገና አዲስ ክርስቲያን መሆኑን ብታውቅም፣ ልታገባው ወሰነች። ቤተ ክርስቲያን ጋብቻቸውን ለመቀበል ፈቃደኛ ባትሆንም፣ በራሳቸው መንገድ ተጋቡ። ከአንድ ዓመት በኋላ እርሷ ልትወልድ አካባቢ ተጣሉና ቤት ውስጥ ትቷት ጠፋ። ማርታ አሁን ብቻዋን ትኖራለች። ማርታን ለዚህ ዓይነቱ ችግር የዳረጋት ግትር የሆነ የትዳር ጓደኛ መስፈርት በመያዝ የጠየቋትን ወንዶች እምቢ ማለቷ ነው። ከዚያም በተስፋ መቁረጥ ስሜት ውስጥ ገብታ ከማይመጥናት የትዳር ጓደኛ ጋር ተጣምራ ችግር ላይ ወደቀች።[31]